# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## ማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮሌጅ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

"ችካል እና እርምጃ "ረጅም ልቦለድን ከልቦለድ አላባዉያን አንፃር

በ

ሰርካዲስ ቢተው

የጥናቱ አማካሪ

ሽኩር ናስር

ነሐሴ 2013 ዓ.ም

# ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድን ከልቦለድ አላባዉያን አንፃር

በ

ሰርካዲስ ቢተው

የጥናቱ አማካሪ

ሽኩር ናስር

ለአርትስ ኦፍ ባችለር ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

ነሐሴ 2013 ዓ.ም

# የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥንታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማመከሪያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም...............................................ፊርማ.........

ይህ በተማሪ ሰርካዲስ ቢተዉ"ችካል እና እርምጃ "ረጅም ልበ-ወለድ ከልበ-ወለድ አላባውያን አንፃር ትንተና በሚል ርዕስ የተሰራውን የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥንታዊ ፅሑፍ  የዩኒቨርስቲውን ጥራት ደረጃ ያሟላ እና ለቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው።ይህም በፈታኝ ኮሚቴ ተረጋግጣል።

ፈታኝ1 ፊርማ

............................................. ..........

ፈታኝ2 ፊርማ

.............................................. ...........

ቀን..........................................

## ምስጋና

በመጀመሪያ እዚህ እንድደርስ የረዳኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። በመቀጠል ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ እንድሰራ የፈቀዱልኝ መምህራኖቼ ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ላገዘኝ አማካሪዬ ሽኩር ናስር ፣በፀሎታቸው ላልተለዩኝ ቤተሰቦች እና ስደሰት ተደስቶ ሲከፋኝ አፅናንቶና የጥናታዊ ፅሁፍ ርዕስ እንደ አማራጭነት ላቀረበልኝ ለዉድ ጓደኛዬ ለፍቅር ፣እንዲሁም እርዳታው ሳይለየኝ ከጎኔ ሳይርቅ መረጃ እና ሀሳብ ለለገሰኝ ለዮርዳኖስ ገረመው እና ሌሎችም ጓደኞቼ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከአላባዉያን አንፃር በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። ጥናቱ የሚያተኩረው ችካል እና እርምጃ ልቦለድ አላባዉያን ላይ ነው።ችካል እና እርምጃ ልቦለድ ሰባቱም አላባዉያን በዉስጡ አሉት እነሱም ታሪክ ፣ትልም ፣መቼት ፣ግጭት ፣ጭብጥ ፣ገፀባህርይ እና አንፃር ናቸው። የጥናቱን አላማ ለማየት የመዛግብት እና የመረጃ ትንተና ተካሂዷል። በተሰበሰበው መረጃ መሰረት አጥኝዋ ችካል እና እርምጃ ልቦለድ ከአላባዉያን አንፃር ምን እንደሚመስል ገልፃለች። ጥናታዊ ፅሁፉንም አግኝተው ለሚያነቡ አንባቢዎች ስለ ልቦለድ አላባዉያን ምንነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

## ማዉጫ

ምስጋና.......................................................................................................................................I
አጠቃሎ.......................................................................................................................................II
ምዕራፍ አንድ.......................................................................................................................................1
1. መግቢያ.......................................................................................................................................1
1.1 የጥናቱ ዳራ.......................................................................................................................................1
1.2. የጥናቱ አላማ.......................................................................................................................................1
1.2.1. የጥናቱ አብይ አላማ.......................................................................................................................................1
1.2.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ.......................................................................................................................................1
1.3. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች.......................................................................................................................................2
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ.......................................................................................................................................2
1.5. የጥናቱ ወሰን.......................................................................................................................................2
1.6. የጥናቱ ዘዴ.......................................................................................................................................2
1.6.1 የጥናቱ አይነት.......................................................................................................................................2
1.6.2 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ.......................................................................................................................................2
1.6.2.1 መዛግብት.......................................................................................................................................2
1.7 የጥናቱ አወቃቀር.......................................................................................................................................3
ምዕራፍ ሁለት.......................................................................................................................................4
2.ንድፈ-ሀሳባዊ ቅኝት.......................................................................................................................................4
2.1.የረጅም ልቦለድ ባህሪያት.......................................................................................................................................4
2.2 የልቦለድ ምንነት.......................................................................................................................................4
2.3. የልቦለድ አላባዉያን.......................................................................................................................................4
2.3.1 ታሪክ.......................................................................................................................................5
2.3.2 ትልም.......................................................................................................................................5
2.3.3 ገፀባህርይ.......................................................................................................................................5
2.3.3.1 የገፀባህርይ ምንነት.......................................................................................................................................5
2.3.3.2. የገፀባህርይ አቀራረፅ.......................................................................................................................................6
2.3.3.3 ገፀ ባህሪያት የሚሳሉበት መንገድ.......................................................................................................................................6
2.3.4. ግጭት.......................................................................................................................................6
2.3.5 መቼት.......................................................................................................................................7
2.3.5.1 አጠቃላይ ና ዉሱን መቼት.......................................................................................................................................7
2.3.6 ጭብጥ.......................................................................................................................................7
2.3.7 አንፃር.......................................................................................................................................8
2.3.7.1 ሁሉን አወቅ አንፃር.......................................................................................................................................8
2.3.7.2 ዉሱን ሁሉን አወቅ አንፃር.......................................................................................................................................8
2.3.7.3 አንደኛ መደብ አንፃር.......................................................................................................................................9
2.3.7.4 ተዉኔታዊ አንፃር.......................................................................................................................................9

2.4 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት .......... 9
ምዕራፍ ሶስት .......... 10
3. የመረጃ ትንተና .......... 10
3.1 .ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ .......... 10
3.2 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከትልም አንፃር .......... 11
3.3. በችካል እና እርምጃ ልቦለድ ውስጥ የገፀባህርያት አሳሳል .......... 12
3.4 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከግጭት አንፃር .......... 17
3.5 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከመቼት አንፃር .......... 19
3.6 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከጭብጥ አንፃር .......... 20
3.7. ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከአንፃር አንፃር .......... 21
3.8 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድን ጠንካራና ደካማ ጎኑን መተንተን .......... 22
ምዕራፍ አራት .......... 23
4.1. ማጠቃለያ .......... 23

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ስነ ጽሁፍ ማለት የሰዉ ልጅ ስሜቱን የሚገለጽበት ደስታውን ሀዘኑን በጽሁፉ መልክ የሚያቀርብበት መንገድ ነው። ይህን ስሜት ለተደራሲያን ሲያደርስ ደግሞ ተደራሲያን የስሜቱ ተጋሪ ወይም አንድ አካል ይሆናሉ ። ስነ ፅሁፍ በዉስጡ የተለያዩ ዘርፎችን ይይዛል ። እነዚህም ስነ-ቃል፣ስነግጥም ፣ልቦለድ እና ተዉኔት ናቸው። ይህ ጥናትም ከእነዚህ የስነፅሁፍ ዘርፎች መካከል አንዱ በሆነው ልቦለድ ልይ ያተኩራል ።

ልቦለድ አንዱ የስነፅሁፍ ዘርፍ ሲሆን በዉስጡ ሰባት አላባዉያንን ይዟል። እነዚህም ታሪክ ፣ ትልም ፣ገፀባህርይ ፣ ግጭት ፣መቼት ፣ ጭብጥ እና አንፃር ናቸው። እነዚህን አላባዉያን ያላሟላ ልቦለድ ልቦለድ ሊባል አይችልም ። ልቦለድ ማለት የደራሲው የምዕናብ ፈጠራ ነው ። ልቦለድ በእዉኑ አለም የሚኖሩ ሰዎችን አስመስሎ በባህሪያቸው በስራቸዉ የሚቀረፁ ናቸው ። ሆኖም በእዉኑ አለም የተፈጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ገና ሊፈጠሩ ይችላሉ ብሎ የሚያስባቸው ክስተቶች የሰዉ ልጅን ደስታና ሀዘን ፣ማግኘት እና ማጣት የሚያሳይ ነው ። በልቦለድ ዉስጥ ደራሲው ማስተላለፍ የፈለገውን ሀሳብ እንደተፈለገው አድረገው ከአንባቢ ዘንድ ያደርሱልኛል ብሎ የማያስባቸዉን ገፀ ባህሪያትን በመፍጠር ስጋ ለብሰዉ መጠሪያ ተሰይሞላቸዉ ፀጋ ተጎናፅፈዉ የሚደሰቱ የሚያዝኑ የሚበሉ የሚጠጡ የሚፋቀሩ የሚጣሉ እና በዛ በቦታው የሚኖሩ በዛን ጊዜ የነበሩ ተደርገው የሚሳሉ የገሀዱ አለም ነፀብራቅ ናቸዉ።በመሆኑም ይህ ጥናት ችካል እና እርምጃ የተሰኘውን ረጅም ልቦለድ ከአላባዉያን አንፃር ይተነትናል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አጥኝዋ ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ያነሳሳት ችካል እና እርምጃ ልቦለድን ከረጅም ልቦለድ አላባዉያን አንፃር መተንተን በሚል ርዕስ ልቦለድ በዉስጡ የሚያካትታቸዉን የአላባዉያን አይነት ለማሳየት በተጨማሪም ችካል እና እርምጃ ልቦለድ ከልቦለድ አላባዉያን አንፃር ተሰርቶበት ባለማወቁ ምክንያት ተደራሲያን ከመፀሀፍ ትምህርት እንዲወስዱ ለማድረግ እና ችካል እና እርምጃ ልቦለድን ማለትም ከታሪክ ፣ ከትልም ፣ ከገፀባህርያት ፣ከጭብጥ ፣ከአንፃር ፣ከግጭት እና ከመቼት አጠቃላይ ከልቦለድ

አላባዉያን አጠቃቀሙን በመተንተን ላይ ያተኮረ ሲሆን ደካማና ጠንካራ ጎኑንም ለማየት ነው።

### 1.2. የጥናቱ አላማ

#### 1.2.1. የጥናቱ አብይ አላማ

ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድን ከረጅም ልቦለድ አላባዉያን አንፃር መተንተን ።

#### 1.2.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ

ችካል እና እርምጃ እረጅም ልቦለድን ከታሪክ ፣ከትልም ፣ከገፀባህርያት ፣ከመቼት ፣ከግጭት ፣ከአንፃር እና ከጭብጥ መተንተን።

## 1.3. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የተለያዩ መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን ያነሳል ። ከእነዚህም ዉስጥ

1. ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ የረጅም ልቦለድ አላባዉያንን ያሟላል ወይ?

2.በዚህ ልቦለድ ዉስጥ መሪ ገፀባሕርያት በምን መልኩ ተስለዋል የሚሉትን ያካትታል ።

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

የጥናቱ መካሄድ በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ። ከእነዚህም መካከል ጥናታዊ ፅሁፉን አግኝተው ለሚያነቡ አንባቢዎች ስለ ልቦለድ አላባዉያን ምንነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል ፤በልቦለድ አላባዉያን ላይ ጥናታቸውን ለሚያደርጉ አጥኚዎች የመረጃ ምንጭ በመሆንም ያገለግላል።

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድን ከልቦለድ አላባዉያን አንፃር መተንተን ። ይሄውም ታሪክ ፤ ትልም ፣መቼት ፣ግጭት ፣ጭብጥ ፣ ገፀባህርይ እና አንፃር በእነዚህ አላባዎች አንፃር ብቻ ትንተናው የሚካሄድ ይሆናል ።

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

### 1.6.1 የጥናቱ አይነት

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ ሚባለዉን የጥናታዊ ጽሁፉ አይነት የሚጠቀም ነዉ ። አጥኝዋ ገላጭ የጥናት አይነት በመጠቀም ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድን ከአላባዉያን አንፃር መተንተን ይሆናል። ገላጭ የጥናት አይነት ማለት የሚሰራውን ነገር ብዙ ሳይለዉጥ እንዳለ በሰው አዕምሮ ዉስጥ ምስልን ሊፈጥር ይችላል ብሎ የሚያስበውን ነገር የሚያቀርብበት ነው።ነገር ግን ስለዛ ነገር ሳያጎላ ሳያሳንስ ለሰው የሚያደርስበት መንገድ ነው። እንደ ያለው እንዳወቀ ሙሉ (2009-40) ገለጻ ተመራማሪው የሚያጠናዉን ባህሪ እንዳለ ትረካዊ በሆነ በአንባቢዉ አእምሮ ዉስጥ ስለ ጉዳዩ ስዕል በሚፈጥር ሁኔታ ባልተጋነነ፣ባልተሞካሸ፣ ባልተንኳሰሰና እዉነታዉን በማያደበዝዝ መልክ ለማቅረብ ያስችላል ።

### 1.6.2 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሰራ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ሊጠቀም ይችላል ። ሆኖም አጥኝዋ መዛግብት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን የምትጠቀም ይሆናል ።

#### 1.6.2.1 መዛግብት

መዛግብት ማለት አንድን ጥናት ለመስራት በሚነሳበት ወቅት ስለሚሰራው ጉዳይ እንደ ኢጋዥ ሊጠቀምበት የሚችለው እንደ መፀሀፍ አንዳንዴም ደግሞ ከሰዉ የምናገኘዉ የመረጃ ምንጭ ነው። ያለው እንዳወቀ ሙሉ(2009-191) ገለፃ"« መዛግብት ተመራማሪው ስላለፈም ይሁን ወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲነሳ ሊጠቀምባቸዉ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸዉ። መዛግብት በፅሁፍ መልክ

ከየቤተመፀሀፍቱ፣ቤተ መዛግብቱ ወይም ከሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎችና እንደ ሁኔታዉም ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸዉ ። ››

አጥኝዋ ይህንን ጥናት ለማጥናት መፃህፍትን ደጋግሞ በማንበብ የተዛማጅ ስራዎችን ቅኝት በማድረግ የምታጠና ይሆናል ።

## 1.7 የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ አወቃቀር በአራት ምዕራፍ የተከፋፈለ ነዉ ። ምዕራፍ አንድ መግቢያ ፣የጥናቱ ዳራ ፣የጥናቱ አላማ ፣የጥናቱ አብይ አላማ ፣የጥናቱ ንዑስ አላማ ፣የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን ያካተተ ሲሆን ምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳባዊ የልቦለድ ምንነትን የያዘ ሰባቱንም የልቦለድ አላባዎችን እነሱም ታሪክ ፣ትልም፣ ገፀባህርይ፣መቼት፣አንፃር ፣ግጭት እና ጭብጥን በዉስጡ የያዘ ነው። ምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተናን ሲይዝ በመጨረሻው ምዕራፍ ማጠቃለያና ዋቢ መፀሀፍትን ይይዛል ።

## ምዕራፍ ሁለት

## 2.ንድፈ-ሀሳባዊ ቅኝት

ከረጅም ልቦለድ ባህሪያት አንፃር የሚሰራ እንደመሆኑ መጠን በተመሳሳይ መረጃ ከልቦለድ አንፃር የሚታዩነጥቦችን መመልከት አስፈላጊ ነዉ።

### 2.1.የረጅም ልቦለድ ባህሪያት

ረጅም ልቦለድ ከስነፅሁፍ ዘርፎች አንዱ ነው። ሆኖም ረጅም ልቦለድ ሰፋ ያለ መጠን ያለዉ ከሌሎች በበለጠ ብዙ ገፀባህርያቶችን የሚያካትት እና ብዙ ቃላቶችን በመጠቀም ለተደራሲያን ሰፋ ባለ መልኩ ያደርሳል። ብርሃኑ ገ/ፃዲቅ (2008-109) "ረጅም ልቦለድ ሰፋ የለ ታሪክ እና ብዙ ገፀባሕርያት ያሉት የኪነጥበብ ስራ ነዉ ። ታሪኩ በተለያየ ቦታዎች እና በተለያየ ጊዜያት ይፈፀማል። ረጅም ልቦለድ ሰፊና ዉስብስብ ግጭቶች ፤ ረጅም ልቦለድ ብዙ ቅርንጫፍ ጭብጦች ፤ብዛትባላቸው ገፆች እና ከ 80 ሺ ባላነሱ ቃላት ይፃፋል ።"

### 2.2 የልቦለድ ምንነት

ይህም ማለት ልቦለድ ሰፋ ያለ በመሆኑ የሰዉን ልጅ ገጠመኞችን አቀናብሮ የያዘና በኪነ ጥበባዊ ቅርፅ የሚቀርብ ፤የሰውን ልጅ ሀዘንና ደስታ ፍቅና ጥላቻ ወዘተ የመሳሰሉ ነገሮችን በዉስጡ የያዘ ነዉ ። ዘሪሁን አስፋው (2005-145)

> ልቦለድ ማህበራዊ ህይወትን በስፋት በሚጥምና በሚስብ ዘይቤ የማሳየት አቅም ያለው
>
> ፣ የሰዉን ልጅ አያሌ ገጠመኞች ማቅረብ የሚችል ኪነ ጥበባዊ ቅርፅ ነዉ ። ከሌሎቹ
>
> የስነ የፅሁፍ ዘሮች የበለጠ ዘላቂነት ያላቸው የተስፋፋና የበለፀጉ የሰዎች ምስሎችን
>
> የመያዝ አቀም አለው። በልቦለድ የሰው ልጅ ሀዘንና ደስታ፣ጥላቻና ፍቅር ፣ ምኞትና
>
> ፍላጎት፣ብልጽግናና ዉድቀት ፣ባጠቃላይ ግብሩና አተያዩ በኪነታዊ ዘዴ ይቀርባል ።

### 2.3. የልቦለድ አላባዉያን

ማለት የልቦለድ አላባዉያን የሚባሉት በልቦለድ ዉስጥ ተያያዥነት ያላቸው ናቸው ። አንዱን ጠርተን ሌላኛውን መተው የማንችል እርስ በርስ የተያያዙ ናቸዉ።ታሪክ ስንል ታሪኩን የሚያስቀቀጥሉልንን ገፀባሕርያትን መጥራታችን አይቀርም ገፀባህርይ ስንልም የሚኖሩበትን ጊዜ እና ቦታ እንጠራለን። እናም የልቦለድ አላባዎች ተያያዥነት አላቸው የተገዳደፉ ናቸው። ዘሪሁን አስፋው (2005-154) "የልቦለድ ፍሬ ነገሮች ወይም አላባዉያን ተብለው የሚታወቁት ታሪክ፣ትልም፣ገፀባህርይ፣ግጭት፣መቼት ፣ጭብጥ እና አንፃር ናቸው። እነዚህ ለአጠናን እንዲያመች ተለይተው ተጠሩ እንጂ በልቦለድ ዉስጥ በተናጠል ወገን ተለይተው ለየብቻቸው የሚገኙ አይደለም ።"

### 2.3.1 ታሪክ

ታሪክ ማለት በልቦለዱ ዉስጥ ምን ያህል የሰዉን ቀልብ የመያዝ አቅም እንለዉ የሚያሳየን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አንድ ሰው ስላነበባቸዉ መፅሃፍቶች የትኛው እንደተመቸዉ እና እንዳስደሰተው ብንጠይቅ ከሁሉም በፊት የዚህ መፀሀፍ ታሪክ ብሎ ነዉ መንገር የሚጀምረው፡፡ እናም ለዚህ ነዉ ታሪክ ለልቦለድ ቀዳሚ ነዉ የተባለው፡፡ ዘሪሁን አስፋው (2005-154)

> ታሪክ ለልቦለድ ቀዳሚ ነገር ነዉ ፡፡ የልቦለድ መስረታዊ ገፅታ አንድ አይነት ታሪክ መተረኩ ነዉ ፡፡ አንድን ልቦለድ ያነበበ ሰው ስለ መፅሐፍ ቢጠየቅ ከሁሉ በፊት አሳዛኝ ታሪክ አነበብኩ ፣ወይም አስደሳች ታሪክ አነበብኩ፣በጣም ጥሩ የፍቅር ታሪክ ነዉ ፣በማለት ታሪኩ ያሳደረበትን ስሜት ነዉ እሚገልፀዉ፡፡

### 2.3.2 ትልም

ትልም ማለት ልክ እንደ ታሪክ የሚነገር ነገር ነዉ ፡፡ ነገር ግን ታሪክንና ትልምን አንድ የማያደርጋቸዉ ነገር አለ፡፡ ይህም ማለት ታሪክ ከአንዱ ጉዳይ ወደ ሌላኛው ጉዳይ እየተተረከ የሚሄድ ሲሆን ትልም ግን ከአንዱ ጉዳይ ወደ ሌላኛው ሲተላለፍ በምን ምክንያት ለምን እያለ የሚጠይቅ ስለሆነ የራሱ የሆነ ምክንያት እና ዉጤት አለዉ፡፡ ለዚህም ነዉ ከታሪክ የሚለየው፡፡ ዘሪሁን አስፋው (2005-158) ገለፃ ትልም ማለት በአንድ ልቦለድ ዉስጥ ምን ? ለምን ተደረገ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘውን መልስ ያካተተ ወይም በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈፀሙ ሁነቶች የተደረጉበትን ምክንያትና የሚያስከትሉትን ዉጤት ጥብቅ ቁርኝት የያዘ የልቦለድ አካል ነዉ ፡፡

### 2.3.3 ገፀባህርይ

ገፀባህርይ ማለት ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ያስተላልፋልኛል ብሎ እስካመነባቸዉ ድረስ በእዉኑ አለም ላይ ያሉትን ሰወች አስመስሎ የሚስላቸዉ የደራሲው የምዕናብ ፈጠራወች ናቸዉ ፡፡ በእዉኑ አለም ዉስጥ እንዳሉ ሰዎችም የሚበሉ የሚጠጡ የሚጣሉ የሚታረቁ የደራሲው የምዕናብ ፈጠራወች ናቸው፡፡ስጋ ለብሰው መኖሪያ ተዘጋጅቶላቸው መጠሪያ ተሰይሞላቸዉ በተፈቀደላቸዉ ጊዜ እና ቦታ ሆነው ታሪኩን የሚያስቀጥሉልን ናቸው፡፡ ብርሃኑ ገ/ፃዲቅ (2008-108) ገለፃ ገፀባህርይ ማለት በልቦለድ ጽሁፍ ደራሲው ከሃሳቡ አመንጭቶ የሚፈጥረው የገሃዱ አለም ሰወች የሚወክሉ ፍጡሮች ናቸው ፡፡ በተጨማሪም ፋንታሁን እንግዳ (2009-25) "ገፀ-ባህርይ የገሃዱ አለም ፍጡራን አካልና አምሳል ተክለው የሚቀርጹ የልቦለድ ፣የተዉኔት ፣የተራኪ ግጥም ፣በጥቅሉ የፈጠራ ስራ ሰወች ናቸዉ በእዉነተኛ በተጨባጩ አለማችን ረጅም፣ አጭር፣ አንካሳ፣ ሸበቶ፣ መልከ ቀና ፣መልከ ጥፉ፣ጥቁር፣ ነጭ፣ እንዳሉ ሁሉ በልቦለድ አለም እነዚህ ሰወች ይገኛሉ ፡፡"

#### 2.3.3.1 የገፀባህርይ ምንነት

ይህም ማለት ስለ አንድ ልቦለድ ሲነገር ተቀርፀው ያሉትን ዋና ዋና የምንላቸውን ገፀባህሪያትን ጠርተን የእነሱ እንደሆነ እንናገራለን ፡፡ ሆኖም እነዛ ሰወች የራሳቸው የሆነ የህይወት መንገድ ያላቸው ሰወች ናቸው ፡፡ ዘሪሁን አስፋው(2005-160) ገፀባሕርያት ምንነት በአንድ ልቦለድ የሚተረክ ታሪክ የማን ነዉ ? የሚል ጥያቄ ሲጠየቅ መልሱ በቀጥታ የእነ እገሌ ታሪክ ነዉ የሚል ይሆናል፡፡ እነ እገሌ ተብለው የሚጠቀሱት ደግሞ የተለያዩ ባህሪያትና የህይወት ገፅታዎች ያላቸው ሰወች ናቸው ፡፡

#### 2.3.3.2. የገፀባህርይ አቀራረፅ

የገፀባህርይ አቀራረፅ ማለት ደራሲው ለአንባቢያን ማስተላለፍ የፈለገውን ነገር ከተፈለገው ቦታ ያደርሱልኛል ብሎ ያሰባቸውን ገፀባህሪያቶችን በመቅረፅ ለአንባቢያን ያደርሳል። ደራሲው ገፀባሕርያትን የሚቀርፀዉ በእዉኑ አለም ዉስጥ ከሚያያቸዉ ሰዎች ባህሪያትንና መልኮችን መነሻ በማድረግ የራሱን ፈጠራና ጥበብ በመጨመር ገፀባህሪያቶችን ይቀርፃል ። ዘሪሁን አስፋው (2005-161)« ደራሲው ገፀባህርይ በሚቀርፅበት ጊዜ ምርጫ ያደርጋል ። ከተመለከታቸዉ ሰወች መሀል ለፈለገው አላማ ግብ መቺ ይሆናሉ ብሎ ያመነባቸውን ወይም ገፀባህርይዉን በዉል ሊያሳዩ ይችላሉ የሚላቸውን የተወሰነ አካላዊና ህሊናዊ መልኮች ብቻ መርጦ ይወስዳል።" በተጨማሪም እንደነ ጫንያለዉ ወ/ጊወርጊስ (2009-34) « ስለ አንድ ገፀባህርይ የጀርባ ማንነት በራሱ ወይም በሌላ ገፀባህርይ አማካኝነት መተረክ፣ ሌላው ስለ ማንነቱ ለማሳወቅ ሲባል የነበረበትንና ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት የሚረዳ መንገድ ነው። »

ከላይ እንደተገለገፀዉ ባህርይ በልቦለድ ዉስጥ እራሳቸውን ወይም ስለ ሌሎች ገፀ ባህርይ ጓደኞቻቸዉ ሊያስተዋዉቁልን ይችላሉ።

#### 2.3.3.3 ገፀ ባህሪያት የሚሳሉበት መንገድ

ገፀባሕርያት በልቦለድ ዉስጥ በሚሳሉበት ጊዜ በአራት አይነት መንገድ ይሳላሉ።አካላዊ አሳሳል በምንለው የገፀባህርይ ዉጫዊ አካሉን ብቻ የሚመለከት ነው። ማህበራዊ አሳሳል ላይም ማህበራዊ ሁኔታው የኑሮ ሁኔታው ያገባ ያላገባ የሚሉትን የሚያካትት ሲሆን ስነልቦናዊ እና ግብረ ገባዊ የምንላቸው ደግሞ ከውጭ አይተን ልናዉቃቸዉ የማንችል ናቸው። ሳሙኤል ተስፋዬ (2010-50)

ገፀ ባህሪያት በአራት ዋና ዋና የገፀ ባህሪያት መሳያ ( መፍጠሪያ ) መንገድ ይዋቀራሉ። እነሱም ፡-

1. የገፀ ባህሪው አካላዊ ማንነት ፡-ቁመት፣ዉፍረት የፊት ከለር ፣
2. የገፀ ባህሪው ማህበራዊ ማንነት ፡-የኑሮ ሁኔታ ፣የሀብት መጠን ፣ያገባ ያላገባ ፣
3. የገፀ ባህሪው ስነ ልቦናዊ ማንነት ፡-ዉስጣዊ የሆነ በዉጪ አይተን እንዲህ ያለ ነው የማንለው

   ፍቅር እና ጥላቻ መከፋትና መደሰት የምንረዳበት አሳሳል ነው

4. የገፀ ባህሪው ግብረገባዊ ማንነት ፡-እንዲሁ ከምናየዉ ከምናዉቀዉ በጣም ወጣ ያለ ባህሪ ያለው። ከመጠን ያለፈ የዋህነት ፣ ከልክ ያለፈ ክፋት ፣ጨቅጫቃ ፣የምንላቸው ናቸው።

ከላይ እንደተገለፀው በልቦለዱ ዉስጥ ገፀ ባህሪያት በአራቱ አይነት መንገዶች ተስለዉ እናገኛቸዋለን።

#### 2.3.4. ግጭት

ግጭት ማለት በልቦለዱ አለም ዉስጥ የተሳሉት ገፀባሕርያት ሁሉም የራሳቸውን ኑሮ በሚኖሩበት ጊዜ በአንድ ነገር ላይ አለመግባባት አለመስማማት ይፈጠራል ። በዚያን ጊዜም ግጭት ዉስጥ ይገባሉ ። ይህም ማለት በእዉኑ አለም ላይም ያለ ማለትም ሁሉም ሰው ኑሮዉንና ፍላጎቱን ለማሟላት ይሮጣል እሱን ጥየ እኔ ማለፍ አለብኝ እኔ ካልበለጥኩ በማለት ግጭት ዉስጥ ይገባሉ ። በልቦለድ አለም ላይም ከእዉኑ አለም ላይ በመሆናቸው አላማቸውን ከግብ ለማድረስ በሚጥሩበት ጊዜ የተለያዩ ግጭቶች ያጋጥሟቸዋል ። ብርሃኑ ገ/ፃዲቅ (2008-108)

‹‹ግጭት አንዱ ገፀባህርይ ከሌላኛው ገፀባህርይ ጋር የሚፈጥረው ንትርክ ፣ገፀባሕርያቱ

ይህን ልፈጽም ወይስ አልፈፅም ብለዉ ከራሳቸው ሀሳብ ጋር የሚፈጥሩት

ቅራኔ ነዉ ። ግጭት የምንላቸውም ሰው ከሰው ጋር፣ ሰው ከራሱ ጋር ፣ ሰው

ከተፈጥሮ ክስተቶችና ገፅታዎች ጋር እና ሰው ከማህበረሰቡ ጋር የሚባሉት

ናቸው ።› በተጨማሪም እንደ ዘሪሁን አስፋው (2005-172) ገለፃ፡-

« ግጭት በሁለት ተፃራሪ ሀያላት መካከል በሚደረገው ትግል አንዱ ሌላኛውን ለማሸነፍ ፣አንዱ ሌላውን ለመጣል ወይም አንዱ በሌላኛው ላይ የበላይነት ለማግኘት ሲጥር ፣ሌላው ላለመሸነፍ ፣ ላለመዉደቅ ወይም ላለመበለጥ ሲጭፈረፈር ይታያል። ግጭት ገፀባሕርያት ከገቡበት ፍልሚያ ማጥ ለመወጣት ሲጣጣሩ፣ሌላ ችግር ሲደነቀርባቸዉ ፣እንደገና ለማርገብ ሲሞክሩ የሚታይበት የልቦለድ አይነተኛ ፍሬ ነገር ነዉ ። »

### 2.3.5 መቼት

መቼት ማለት በልቦለዱ ዉስጥ ታሪኩ የተፈፀመበትን ጊዜዉን እና ቦታውን የሚነግረን ማለት ነዉ ።መቼት መቼ እና የት የሚል ሲሆን ታሪኩ የተፈፀመበት ትልቁ ቦታ ፣ታሪኩ የተፈፀመበት ትንሹ ቦታ እና ታሪኩ የተፈፀመበት ዉስን እና አጠቃላይ ጊዜዉ ማህበራዊ ሁኔታውን ሁሉ የሚገልፅ ነው። ብርሃኑ ገ/ፃዲቅ (2008-108) « መቼት ማለት መቼ እና የት ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገነባ ነዉ የልቦለዱ ታሪክ የተፈፀመበት ጊዜ እና ቦታ ማለት ነዉ ። »

#### 2.3.5.1 አጠቃላይ ና ዉሱን መቼት

አጠቃላይ ና ውሱን መቼት ማለት በልቦለዱ ዉስጥ ታሪኩ በሚካሄድበት ጊዜ ትልቁ ድርጊቱ የሚካሄድበት ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም ድርጊቱ የሚፈፀምበት ትንሿ ቦታ እና ትንሿ ጊዜ ጊዜም በሚባልበት ማምሸት መንጋቱን እና ሰዓትን ሁሉ የሚያካትት ነው። ፋንታሁን እንግዳ(2009-14)

« ብዙ ጊዜ በአንድ፣የልቦለድ፣የፊልም እና የተራኪ ግጥም ስራ ዉስጥ አጠቃላይና ዉሱን

የመቼት አይነቶች በአንድነት ተብራርተዉ ተገልፀዉ ይቀርባሉ። አጠቃላይ መቼት በአንድ

የተወሰነ ድርሰት ዉስጥ የሚገኘው ትልቁ የድርጊት መከወኛ የጊዜ መለኪያና ትልቁ

የድርጊቱ መከወኛ ቦታ ነው።ዉሱን መቼት በሌላ በኩል በአንድ በተወሰነ ድርሰት ዉስጥ

የሚገኘው ትንሹ የድርጊቱ ጊዜና ትንሹ የድርጊቱ መከወኛ ቦታ ነዉ ። »

አጠቃላይና ዉሱን መቼት ማለት ታሪኩ የተፈፀመበትን ከትልቁ እስከ ትንሹ ሁለቱንም በአንድነት የያዘ ነዉ ።

### 2.3.6 ጭብጥ

ጭብጥ ማለት ልቦለድ በሚፃፍበት ጊዜ ሊነግር የፈለገው አላማ አለው።ይህን አላማም በታሪኩ ሂደት በገፀ ባህሪያቶች ዉስጥ ደራሲው ከሚያዉቀዉ የህይወት ገጠመኞች ጋር እና ለህብረተሰቡ ያለውን አስተሳሰብና እዉቀት መሰረት አድርጎ በልቦለዱ ዉስጥ የሚቀርፀዉ ዋና

አላማ በልቦለዱ ዉስጥ ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና ሀሳብ ነው። ብርሃኑ ገ/ፃዲቅ(2008-108)« ጭብጥ ከአጠቃላይ የልቦለዱ ታሪክ ተጨምቆ ወይም ተፈልቅቆ የሚወጣ የልቦለዱ መልዕክት ነዉ ። »

ይህም ማለት በልቦለዱ ዉስጥ ማስተላለፍ የየፈለገው ዋና ሀሳብ ነዉ ።

## 2.3.7 አንፃር

አንፃር ማለት ተራኪ እንደማለት ነዉ ። ይህም ማለት ታሪኩን የሚተርክልን ነዉ ነገር ግን በታሪኩ ዉስጥ የእሱም ታሪክ ሊኖር ይችላል ። ካለበት የራሱንም ታሪክ የሌሎችንም ከሱ ጋር የሚያመሳሉትን የሚያቀርበው። ዘሪሁን አስፋው(2005-190) ማንኛውም ልቦለድ በደራሲው ና በአንባቢዉ መካከል ሆኖ ሁነቶችን የሚገልፅና የሚተረጉም አልፎ አልፎ በግልጽ አብዛኛውን ጊዜ ግን በዉስጠ ታዋቂ የሚኖር የታሪኩን ሂደት እየተከታተለ የሚያቀርብ ተራኪ አለው ።በዚህ አይነት ደራሲያን መርጠው የልቦለዳቸዉን ታሪክ የሚያቀርቡባቸዉ አራት መሰረታዊ የአንፃር አይነቶች መኖራቸዉ ይታወቃል ። እነሱም ሁሉን አወቅ፥ ዉሱን ሁሉን አወቅ፥ አንደኛ መደብና ተዉኔታዊ ተብለው ይጠራሉ ።

### 2.3.7.1 ሁሉን አወቅ አንፃር

ሁሉን አወቅ አንፃር ማለት በልቦለዱ ዉስጥ አንዳንዴ በዉስጠ ታዋቂነት አንዳንዴ ደግሞ በግልጽ ሆኖ የሚተርክልን ነው።ሆኖም ሁሉን አወቅ አንፃር በልቦለዱ ዉስጥ ያሉትን የሁሉንም ገፀባህሪያትን ግንኙነት የኑሮ ሁኔታ ሁሉንም ነገር ጠንቅቆ ያዉቃል። ዘሪሁን አስፋው (2005-191)

«ይህ ለተራኪዉ ሰፊ ነፃነት የሚሰጥና በሶስተኛ መደብ የሚተረክ የትረካ አንፃር ነው። ቃሉ እንደሚያመለክተው ተራኪው በልቦለዱ ዉስጥ የሚከናወነዉን ሁሉ ፤ የገፀ ባህርያቱ ማንነት ፤ ስሜትና ሀሳብ ፤ ምኞትና ፍላጎት በሚገባ ያዉቃል ። ገፀ ባሕርያቱ በልቦለድ ህይወታቸው የሚገጥማቸውን እጣ ፋንታ በዉል የተገነዘበና ሚስጥራቸውን በዝርዝር የሚያዉቅ በመሆኑ ገመናቸዉን አዉጥቶ የማሳየት አቅሙ ሰፋ ያለ ነዉ ።»

ሁሉን አወቅ አንፃር ማለት ተራኪው በልቦለዱ ዉስጥ ያሉትን ገፀባሕርያት ስለነሱ ሁሉንም ነገር የሚያዉቅ ምን እንደሚያወሩ ምን ሊገጥማቸዉ እንደሚችል ባጠቃላይ ለተራኪዉ ሰፊ ነፃነትን የሚሰጥ የትረካ አይነት ነዉ ።

### 2.3.7.2 ዉሱን ሁሉን አወቅ አንፃር

ዉሱን ሁሉን አወቅ አንፃር ማለት ደግሞ ከስሙ እንደምንረዳው ስለ ገፀባህሪያቶች የተወሰነ ነገር ብቻ የሚያዉቅ ምን ሊገጥማቸዉ እንደሚችል የማያዉቅ የተገደበ ነፃነት ያለው የተራኪ አይነት ነው። ዘሪሁን አስፋው (2005-195 ) « ዉሱን ሁሉን አወቅ አንፃር እንደ ሁሉን አወቅ አንፃር በሶስተኛ መደብ የሚተረክ የሁሉንም ገፀባሕርያት ስሜት አስተሳሰብም ሆነ ፍላጎት አያዉቅም ። የራሱንም ፍልስፍና አስተያየት የመንዛት አቅሙ የተገደበ ነዉ ። »

### 2.3.7.3 አንደኛ መደብ አንፃር

አንደኛ መደብ አንፃር ማለት ተራኪው የራሱን ታሪክ የደረሰበትን ችግር ፣የህይወት ዉጣ ዉረድ ፣መዉደድ መጥላት ወዘተ እና ከራሱ ዉጪ የሆኑ ገፀባህርያትንም እንዲህ ሆኑ እንዲህ ያለ ችግር ደረሰባቸው እያለ የሚተርክልን የአንፃር አይነት ነዉ ። ዘሪሁን አስፋው (2005-196) ተራኪው " እኔ " ይህን አየሁ፥ ይህን ተመለከትኩ እገሌ የሚባለው ገፀባህሪ በዚህ ወጣ ፥በዚያ ወረደ ፥ እገሌ ደግሞ እንዲህ ያለ ችግር ደረሰበት ፥ እገሌና እገሌ ተፋቀሩ ፥ ተጣሉ ወይም በራሴ ላይ እንዲህ ያለ ድርጊት ተፈፀሙብኝ ። እንትናን ወደድኩ ፥ጠላሁ ወዘተ እያለ የሚተርክበት የአንፃር አይነት ነዉ ።

### 2.3.7.4 ተዉኔታዊ አንፃር

ተዉኔታዊ አንፃር ማለት ተራኪው ስለ ገፀባሕርያት ምንነት እዉቅና የለዉም በዉስጠ ታዋቂነት የሚኖር ነው። ዘሪሁን አስፋው(2005-200) የተዉኔታዊ አንፃር ተራኪው በገፀባህሪያቱ ድርጊትም ሆነ በሁነቶች ምንም አይነት አስተያየት የማይሰጥበት የአንፃር አይነት ነው። በታሪክ ዉስጥ የሚከናወነው ድርጊትም ሆኑ የገፀባህርያት ግንኙነቶች ወይም የሚገቡባቸዉ ሁኔታዎች እንዳሉ ነው የሚቀርበው ።

## 2.4 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

2009 ዓ.ም ዋለልኝ ፍቃዱ ነጋ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ጥናታዊ ፅሁፍ የአስመራ ዘንባባዎች ረጅም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ ከችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከልቦለድ አላባዉያን አንፃር አንድ የሚያደርጋቸው ሁለቱም ከገፀባህሪያት አሳሳል አንፃር የተሰሩ ሲሆኑ ልዩነታቸው ግን አጥኝዋ የምታጠናዉ ጥናት ችካል እና እርምጃ የሚለዉን ከሙሉ ልቦለድ አላባዉያን አንፃር የተሰራ ሲሆን የአስመራ ዘንባባዎች ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ብቻ ተሰርቷል ።

# ምዕራፍ ሶስት

# 3. የመረጃ ትንተና

## 3.1 .ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ

ተሰማ የተወለደው አሰላ ወህኒ ሰፈር ሲሆን አባቱ የሞተበት በልጅነቱ ነው።ተሰማም በጠዋት እየተነሳ ስራ እየሰራ እናቱም ያለ ማንም እጋዥ ብቻዋን ለፍታ አሳደገችው ። ተሰማ መንበረ የምትባል አብሮ አደግ ጓደኛ አለችው ።የተሰማና የመንበረ የትምህርት ደረጃቸዉ አንድ ባይሆኑም ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመጡ አይለያዩም ። የመንበረ ሁሉም ቤተሰቦቿ በህይወት አሉ የአባቷ መንትያ የሆነ አጎትም አላት።

ተሰማ በታሪክ ትምህርት ተመሮ የመመረቂያ ፅሁፍ ለመስራት መረጃ ሲያሰባስብ ከዶክተር ጀምበሩ ጋር ተዋወቁ።"ተሰማ እባላለሁ። የታሪክ ትምህርት ክፍል የአራተኛ ዓመት ተማሪ ነኝ። የመመረቂያ ጥናቴን በአክሱም የድንጋይ ላይ ፅሁፎች ላይ እየሰራሁ ነው። እርስዎ በዚያ ላይ ስለሰሩ እንዲያማክሩኝ ፈልጌ ነው። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 18)

ተሰማ በታሪክ ትምህርት ተመርቆ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ በመምህርነት ተቀጠረ።" ዩኒቨርሲቲ ማስተማር እንደጀመረ በዩኒቨርስቲው ዉስጥ የሚያስተምሩና በዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዉሰጥ የሚሰሩ የአማራ ብሄረሰብ ተወላጆች ለአማራ ህዝብ መብት የሚታገል የፖለቲካ ድርጅት ለማቋቋም እየሰሩ ነበር።

"እኔ በብሄርና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ፖርቲ ለመመስረት አልሆንም ፤ለማፍረስ ካልሆነ። ስለዚህ ተዉኝ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 39)

ከመንበረ ጋርም ከአብሮ አደግ በላይ የፍቅር ጓደኛሞች ሆነዋል ። ተሰማ ነፃ የትምህርት እድል አግኝቶ ሊሄድ ሲል የትምህርት ክፍሉ ሀላፊ የሆኑት ዶክተር ይመር እንዳይሄድ ከለከሉት ።

ተሰማም በራሱ ፈቃድ እምቢ ብሎ ኖርዌይ ሄደ ። ኖርዌይ በገባ በማግስቱ የአባቱ ወገኖች በዘር እንዲደራጅ ጠየቁት።እሱ ግን ሊቀበላቸዉ ፈቃደኛ አልሆነም። እንዲህ አይነቱ ጥያቄ አዲሱ አልነበረም ከዚህ በፊትም ተጠይቆ ያዉቃል።

የተሰማ ጓደኛ የሆነው ጋናዊው ኮጆ ለመስከ ስራ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ተሰማም በዚህ አጋጣሚ ስራ አግኝቶ ነበር ።ተሰማ ለመንበረ ስልክ ሲደዉልላት አታነሳም።

መንበረ ከትምህርቷ ጎን ለጎን ክረምት ክረምት የኮምፒዉተር ትምህርት ተምራ ሰርተፊኬት አላት ። በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ስትማር በደረሰባት ችግር ምክንያት ትምህርቷን አቋረጠች።

ተሰማ በሶስት ዓመት ቆይታ ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። እናቱን፣ መንበረን የመንበረን ቤተሰቦች በሰላም ተገናኙ ። ነገር ግን መንበረ ወንድ ልጅ ወልዳ አገኛት ። ከማን እና ከየት እንደወለደችዉ ግን ከሷ ዉጪ ማንም አያዉቅም ። ተሰማም ያየውን ማመን አቃተው ደህንነታቸውን ጠየቀ።

ተሰማም ትቶት የሄደዉን ስራ መመለስ እንደሚፈልግ ለኮሌጁ ዲን ማመልከቻ አስገባ።ዶክተር ይመር የተሰማ ድፍረት አናዶታል።ተሰማ ወደ ስራ ገበታው ተመለሰ የስራ ባልደረባ ከሆነው ከዶክተር ጀምበሩ ጋር ጓደኝነታቸዉን ቀጠሉ። ዶክተር ጀምበሩ ከተሰማ ሌላ የስራ ባልደረባ የተዋወቃት ፅጌ የምትባል ጓደኛ አለችው። እና ሁለቱንም አስተዋወቃቸዉ ። የተዋወቁ ጊዜ ግን ፅጌና ተሰማ በዘር ፣በብሄር ይጋጫሉ ። ነገር ግን ከቀናቶች በኋላ መግባባት ጀመሩ ።

በዚህ ሁኔታ እንዳሉ ፅጌ የትምህርት እድል መጥቶላት ኒዩወርክ ሄደች። ተሰማ ጠዋትና ማታ መንበረን ያስባል ።

ፅጌም የትምህርት ጊዜዋን ጨርሳ ስትመለስ ጓደኝነታቸዉን ቀጠሉ። ስለመንበረ ያጫዉታታል እሷም የቃል ኪዳን ፍቅረኛ እንዳላትና ቀለበት እንዳደረገላትም ያወራሉ። ነገር ግን ሁለቱም ተግባብተዋል ፣ተዋደዋል በፍቅር ተሳስበዋል

። በዚሁ ሁኔታ ላይ እያሉ ኮቪድ 19 ወደ ሀገራችን ሲገባ መንበረ እና ልጂ በኮቪድ ይያዛሉ ። ዮዲት ለተሰማ ደዉላ መንበረና ልጂ በኮቪድ እንደተያዙ እና ልጂ እንደሞተ ነገረችው ። ተሰማ በሰማው ነገር አዘነ ። መንበረም አገግማ ስትወጣ ልጂን ለማየት ብትጠይቅም የህክምና ባለሙያዎች እንድታየዉ አልፈቀዱላትም ። እሷም ልጂን ሳታየዉ መምጣቷን ባትወደዉም ወደቤቷ ተመለሰች። በተመለሰች በማግስቱ ያልጠበቀችው መከራ ፤ዮዲት የልጂን ሞት አረዳቻት ። መንበረም የሰማችዉን ነገር ማመን አቃታ በሃዘን ተዳከመች ። ነገር ግን አምኖ ከመቀበል ዉጪ ሌላ አማራጭ አልነበራትም ።

ተሰማም የተፈጠረዉን ሁሉ ለፅጌ ነገራትና ሊጠይቋት አብረው ሄዱ። ከዛም ተሰማ ለመንበረ ያለዉን ክብርና ፍቅር ስታይ ፅጌ ቀንታ ወጥታ ትሄዳለች ። መንበረም ከስራ ዉጪ ሌላ ግንኙነት እንዳላቸው ጠረጠረች። ፅጌም ከማን ጋር አብራ መኖር እንደምትፈልግ መወሰን ያቅታታል ተሰማን ማጣት አትፈልግም ። ቀለበት ካሰረላት ፍቅረኛዋ ጋር አብራ መቀጠል እንደማትፈልግ ነገረች። መህሪንም የሰርጋቸዉን ቀን ሲናፍቅ የነበረዉን ህልሙን አጨለመችበት ።

መንበረ እና ዮዲት ቤተሰብ ለመጠየቅ ሄደዉ ልጅ የወለደችው አጎቷ ደፍሯት እንደሆነና ልጁም የአጎቷ እንደነበር ነገረቻቸ። የተሰማ እናትም ሰዉየዉን ገድለው በኩራት እስር ቤት ይገባሉ። ተሰማም በመንበረ ላይ የደረሰባትን ጥቃት ሲያዉቅ ከልቡ አዘነ ። መንበረንም አብረው መቀጠል እንደሚፈልግ አጫወታት እሷ ግን ከወንድምነት ያለፈ የፍቅር ግንኙነት እንዲኖራቸው እንደማትፈልግ ነገረች።

## 3.2 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከትልም አንፃር

መንበረ በመደፈሯ ምክንያት ትምህርቷን አቋረጠች። "በሚቀጥለው አመት ያቋረጥሽውን ትምህርት ትጀምሪያለሽ። እኔ አስተምርሻለሁ። "

"እኔ? ትምህርት? ተማርኩ እኮ። በቃኝ። ህይወት ዲግሪ በዲግሪ አደረገችኝ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 310)

መንበረ ኮሮና ሲገባ የህፃናት ማዋያዋን ባለመዝጋቷ ምክንያት ልጂ እና እሷም በኮሮና ተያዙ የልጂ ህይወትም በኮሮና ምክንያት አለፈ። "ትሂድ፤ ትየዉ እንጂ!እናት የልጂን መቃብር ሳታይ ፣እርሟን ሳታወጣ። ስታነባ ትኑር ብላችሁ ነው? ያሳርፉታል ወዲያው እርፍ ትላላች። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 249)

መንበረ በመደፈሯ ምክንያት ከተሰማ ጋር ከፍቅር ጓደኝነታቸዉ ተለየች። "ውይ ምን አልኩህ። ከህፃናት ዉጪ ማንም በህይወቴ ዉስጥ እንዲኖር አልፈልግም። አንተ ወንድሜ ነህ። ለራሴ ማሰብ ህፃናትን መንከባከብ፤ በቃ። (ችካል እና እርምጃ ገፅ 311)

አቶ ተመስገን መንበረን በመድፈራቸዉ ምክንያት ህይወታቸው በሰው እጅ አለፈ። "እረ ዝም አትበሉ! ወርቁ። ልጆቹ ተለክፈዋል። ወይዘሮ እልፍነሽ ፣"

ማንም ከቆመበት አልተንቀሳቀሰም።

"በሉ ተዉት ፤ኮታቸዉን ከወንበሩ መደገፊያ ላይ መዥርጠው ሊወጡ ሲሉ ፣የተሰማ እናት ከበሩ መዝጊያ ስር የሰብስቤን ጠገራ መዘው ጆሮ ግንዳቸው ላይ አሳረፉት ፤እንደተቆረጠ ዛፍ ዥዋዋ ብለው በጀርባቸው ወደቁ። (ችካል እና እርምጃ ገፅ 300)

## 3.3. በችካል እና እርምጃ ልቦለድ ውስጥ የገፀባህርያት  አሳሳል

ስለሆነም በተከታይነት በልቦለዱ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ገፀባህርያትን ከአራቱም የገፀባህርያት አሳሳል ደረጃ አንፃር ተተንትነው ቀርበዋል።

በችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ዉስጥ ብዙ ገፀ ባህርያትን ያካተተ ሲሆን  ዋና ዋና ገፀባሕርያትን ብቻ ይተነትናል ። ገፀባሕርያት እራሳቸውን አንዳንዴ ደግሞ ሌሎቹን ሊያስተዋዉቁልን ይችላሉ ።  አካላዊ የገፀባህርያት አሳሳል ከስሙ እንደምንረዳው የገፀባህርያቱን ዉጫዊ አካላቸዉ ላይ ብቻ የሚያተኩር ነዉ ። የገፀባህርያት መልክ፣ አካል ፣ ቅጥነት ፣ ዉፍረት ወዘተ ከላይ ሊታይ በሚችለው ላይ ብቻ ነዉ ትኩረቱ ። ማህበራዊ የገፀባህርያት አሳሳል ደረጃ ደግሞ የገፀባህርያት ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነት የኑሮ ደረጃ ፣ የትምህርት ደረጃ ያካተተ ነዉ። ስነ ልቦናዊ የገፀባህርያት የአሳሳል ደረጃ ደግሞ ከላይ አይተን የማናውቀው የገፀባህርይ ዉስጣዊ የሆነ ፍላጎት ና ምኞት ነዉ ። ግብር ገባዊ የአሳሳል ደረጃ ደግሞ እንደ ስነ ልቦናዊ የአሳሳል ደረጃ ሁሉ ዉስጣዊ ነዉ ። የገፀባህርያት ደግነት ፣መጥፎነት ወዘተ ነገሮችን አንባቢ በደምብ እንዲረዳ ያደርጋል። ችካል እና እርምጃ ዉስጥ ያሉ ገፀባሕርያትም በዚህ መልኩ ተስለዋል ።

**ተሰማ**

**አካላዊ አሳሳል**

ተሰማ ፀየም ያለ መልከ መልካም ረዘም ያለ ቁመና ያለዉ ነዉ ። "የሆነ ነገሩ ስቧታል ። ቁመቱንና ጠይምነቱ ይሆን ? ሊሆን አይችልም ? ታየዋለች ።" (ችካል እና እርምጃ ገፅ 153) እንዲህ ሲል ፅጌ የተባለችው ገፀባህርይ የተሰማን መልክ ጠይም እንደሆነና ቁመቱ ረጅም እንደሆነ ታስተዋዉቃለች ።

"የምትሆነዉን ማሰብ ይከብደኛል። "

ዞር ብሎ ተመለከታት። አይኖቹ ድልህ መስለዋል። እንደ ማግኔት የሚስባት ተጫዋችነቱና ቀልዱ የለም። ያደገው ፂሙ ወንዳ ወንድነቱን አጉልቶታል ፤

(ችካል እና እርምጃ ገፅ 233)ይህን ሲለን የተሰማን ደንደን ያለ ሰዉነት  እና ረዘም ያለ አቋም  ያለው መሆኑን ገልፆታል።

**ማህበራዊ አሳሳል**

የወይዘሮ እልፍነሽ ብቸኛ ልጅ የሆነ ወጣት በታሪክ ትምህርት ዲግሪ ያለው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት የሚሰራ ፣ ያላገባ ከሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታ ያለው ነዉ ። "ሁለተኛ ዲግሪ እያለህ ፣ ሌላ ሁለተኛ ዲግሪ ቅንጦት ነዉ ።

"መማር ቅንጦት የሚሆነው እንዴት ነዉ ? "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 24) ተሰማ የተማረ እንደሆነ ገልፆልናል ።

**ስነ ልቦናዊ አሳሳል**

"አለመፍቀዱን እንጂ ፣ ያልተፈቀደበት ምክንያት አልተገለፀም ። " ምክንያቱን በኢሜይሉ ላይ ያልተገለፀው ፣እየተመፃደቀ በራሱ አንደበት ሲነግረው ፣' እባክህ ' እንዲለዉ ፣ ቀጥ ያለ ስብዕናውን እንደ ደጋን ሊያንብጠዉ እንደሆነ ገብቶታል ። (ችካል እና እርምጃ ገፅ 24) ሲል  በአቋሙ የሚፀና ለማንም እንደማያጎነብስ ይነግረናል ።

**ፅጌ**

**አካላዊ አሳሳል**

በደምብ ከተገለፁት መካከል የመጀመሪያዋ ነች ። ፅጌ ረጅም ቁመና ያላት አይን ዉስጥ የሚገባ የሰዉነት አቋም ያላት የሚያምር ፀጉር እና አይኗ ፣ የታችኛው ከንፈሯ የዉበቷ መገለጫዎች ናቸዉ ። " ዉብ ናት! ፀጉርዋ እንደፈጠረው ጠቁሮ ፣ በቀለም ተዥጎርጉሮ ፣ ፈርዛዉ ተንጨባሮ ፣ ተተኩሳዉ ተዘናፍሎ ፣ ያደረገችውን ሁሉ ሆኖ ያምርባታል ። ' እንደ ሳምሶን ጉልበት ዉበትሽ ፀጉርሽ ላይ ነው ' ይላታል ፤ መሀሪ ። የምሽትን ዉበት ከሙሉ ሰማይ እንደነጠቀ ሙሉ ጨረቃ አይኗ የፊቷን ዉበት ብቻውን ሊጠቀልለዉ ፣ከታችኛው ከንፈሯ ጋር እልህ ተያይዟል ። ስለ ፅጌ ዉበት ማዉራት ከአንገቷ በላይ ስለ ፀጉሯ አይንና ከንፈሯ ፣ ከአንገቷ በታች እንደ አንቴና ከዳሌዋ ላይ ተመዞ ስለቀረዉ ሸንጥና ወገቧ ፣ ንጥቅ ንጥቅ ስለሚለው አረማመዷ ማዉራት ነው ። አይኖቿ ነፍስን በብርሀን ይሰረስራሉ ። የታችኛው ከንፈሯ አይኗ እንደሆነው ይሆናል ። ስትፈዝ ስትመሰጥ ይወድቃል ። ስትሸኮረመም መሃል ላይ እንደ ኩይሳ ይከመራል የላይኛው ከንፈሯን ለዉበት አልፈጠረዉም ፣ እንደ ስስ መጋረጃ ጥርሷን ሸፍኖ የታችኛውን ከንፈሯን ያጅባል ፤ እድሜ ለታችኛው ከንፈሯ ልብ የሚለው የለም ። " (ችካል እና እርምጃ ገፅ 161) እንዲህ ሲል ስለፅጌ ዉበት ነግሮናል ። በመሀሪም ስለእሷ ብዙም ባይሆን አስተዋዉቆናል ።

**ማህበራዊ አሳሳል**

ፅጌ ወጣት በቋንቋ ትምህርት ዲግሪ ያላት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋ የመምህርነት ሙያ የምትሰራ ፣ የፍቅር ጓደኛ ያላት ከሰው ጋር የምትግባባ ናት ። "ትዳር ማለትህ ከሆነ ጨ፣ወደ ለንደን ሲሄድ ቀለበት አድርገናል ። " (ችካል እና እርምጃ ገፅ 154) እንዲህ ሲል በሰርግ እንዳልተጋቡ ገና አብረው እንዳልሆኑ ያሳያል ።

**ስነ ልቦናዊ አሳሳል**

ለነገሮች ፈጥና መልስ የምትሰጥ ነገር የሚደጋግምባትን ሰዉ የምትጠላ ስልቹ ናት ።

**መንበረ**

**አካላዊ አሳሳል**

መንበረ አጠር ያለች ፣ ለስላሳ ፀጉር ፣ ድርብ ጥርስ ያላት ስትስቅ የምታምር ትንሽ የፊት ገፅ ያላት ናት ።

" ገና ሶስተኛ ክፍል እያለች ትምህርት ቤት ፣ ድርብ ጥርስ ይሉኛል ። እማዬ አስነቅይልኝ ። አየሽ እግዜር ጉንጭን ሰርጉዶ ብቻ እንዳይመስልሽ ፣ ሲለው ጥርስ ደርቦም ያስጌጣል ። ይንቀልሽ ! ደግሞ አስነቅይልኝ ። ድርብ ጥርስሽ - ዉበትሽ ነው ። ብለዋታል ። እዉነትም ድርብ ጥርሷ የሳቋ አስተዋዋቂ ፣ የዉበቷ የወርቅ ዘርፍ ነው ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 45) ይህን ሲለን መጀመሪያ መንበረ ራሷን እንዳስተዋወቀች በመቀጠልም በሌሎች ገፀባሕርያት ይነግሩናል ድርብ ጥርስ እንዳላት ነግሮናል። "እጇን ሳብ አድርጎ ሲያስጠጋት ደረቱ ላይ ክልብስ አለች ። እቅፍ አደረጋት ። ማጎንበስ ሲል ጭንቅላቷ ላይ አገጩ አረፈ ። የሉጫ ፀጉሯ ልስላሴ ማቆጥቆጥ የጀመረ ሪዙን ዘልቆ ተሰማው ። " (ችካል እና እርምጃ ገፅ 32) እንዲህ ሲል መንበረ ፀጉሯ ለስላሳ እንደሆነ ቁመቷም አጠር ያለች መሆኗን አሳዉቆናል ።

**ማህበራዊ አሳሳል**

ወጣት ያላገባች የአንድ ልጅ እናት ፣ በኮምፒውተር ትምህርት ሰርተ ፍኬት ያላት ፣ያልተሰላጠነች የህፃናት ማዋያ እየሰራች የምትኖር ከሰው ጋር የምትግባባ ናት ። "ልጆችም እኮ ያለ እሷ እምቢ አሉ ፣ ሶስት ልጅ ይቻላል ? በዚያች ጠባብ ክፍል ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 31) ከሰው ጋር እንደምትግባባና በሰው ዘንድም ተወዳጅ እንደሆነች ያስረዳል።

ስነ ልቦናዊ አሳሳል

አስተዋይ ለነገሮች የማትቸኩል የተረጋጋች አገቷ ደፍሯት ለአራት አመት ያክል ለማንም ሳትናገር በደሏን ያለማንም አፅናኝ በዉስጧ አምቃ ያቆየች ነገሮችን በእርጋታ የምትመለከት ናት ።

**ወ/ሮ እልፍነሽ**

**አካላዊ አሳሳል**

ረዘምና ቀጠን ያሉ የሰዉነት አቋም ያላቸው እየድሜያቸዉም በሰል ያሉ ከመሆናቸው የተነሳ ወገባቸውን ማሰር የሚያዘወትሩ ናቸው ። "የተሰማ እናት መንበረ ትከሻ ላይ እጃቸውን ጣል አድርገው ወደ ቤት ሲገቡ ። የለበሱት ረዥም ቀሚስ የበለጠ አስረዝሟቸዋል ። የመቀነታቸዉ ቀይ ጥለት የአረማመዳቸዉን ስልት ጠብቆ እንብርታቸዉ ላይ ይወዛወዛል ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 83) እንዲህ ሲል ገልጿቸዋል ።

**ማህበራዊ አሳሳል**

ያገባች የተሰማ እናት ከሰው ጋር ቶሎ የማይግባቡ ተሳዳቢ የፈረንጅ ላሞችን እያረባች የምትኖር ናት።

**ስነ ልቦናዊ አሳሳል**

ለሰው ያላቸውን ፍቅር በስድብ የሚገልጹ ተሳዳቢ በሆዳቸው ነገር የማይዙ ናቸው። " ከመንበረ ቤተሰቦች ሌላ የተሰማን እናት በእርግማን የተለወሰ አነጋጋር ችሎ የተጎራበታቸዉ የለም ። ምነው የአፋን ትታችሁ የልቧን ንፅህና ብታዩት ፤ ልምድ ሆኖባት እንጂ ። " (ችካል እና እርምጃ ገፅ ) እንዲህ ሲል ገልጿቸዋል ።

**አቶ ተመስገን**

**አካላዊ አሳሳል**

አቶ ተመስገን ፊታቸዉ ላይ ጠባሳ ያለባቸው ደንዳና ሰዉነት ያላቸው ናቸው ። " አየህ አንተ ልብስ የሰጠኸው ለመንትያ ወንድሙ ነው ።

ለፈይሳ ፣ እኛም በፊት እንዲህ እንወነባባድ ነበር ። አሁን በዚህ ጠባሳ እንለያቸዋለን ። "( ችካል እና እርምጃ ገፅ 63) ሲባል አቶ ተመስገን ጠባሳ እንዳለባቸው ይነግረናል ።

**ማህበራዊ አሳሳል**

ልጅ የሌለው /መካን ነጋዴ የልብስ ጣቃ እየሰራ የሚተዳደር ። " ፈጣሪዬ ቅጣቴን ሲያከብደዉ ልጅ ከልክሎ ፤ የልጅ ፍቅሬን አሸከመኝ ይላሉ ። "(ችካል እና እርምጃ ገፁ 52) ይህን ሲለን ልጅ እንደሌለው ነግሮናል ። " አሰላ ከተማ የእሳቸውን የሚያህል የጣቃ ሱቅ ያለው የለም ። በዚያ ላይ ፈጣሪ ከሀብት አስቀድሞ ቸርነትን ሰጥቷቸዋል ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 41) ይህን ሲል በዚያች ከተማ ከሚኖረው ህብረተሰብ የተሻለ የኑሮ ጀረጃ ያላቸው እንደሆኑ ይነግረናል ።

**ስነ ልቦናዊ አሳሳል**

እራስ ወዳድ የሆኑ የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ ሰዉን የሚጎዱ ናቸው ።

**ዮዲት**

**አካላዊ አሳሳል**

ዮዲት ቀይ እና ትንሽ የፊት ገፅ ያላት፣ ወፈር ያለ የሰዉነት አቋም ያላት ፣ ከርዳዳ እና አጭር ፀጉር ያላት ፣ የራሷ ያልሆነ ፀጉር መጠቀም ታዘወትራለች ። " ዱባይ አራት አመት ቆይታ ፣ቀልታና ደንደን ብላ መጣች ። በአይነቱ ዊግና የተሸለተ የሰው ፀጉር ይዛ መጣች ። ከርደድ ያለዉ አጭር ፀጉሯ ነበር የነመንበረ እህት ያለመሆኗን ሲያሳብቅባት የኖረው ። ተበቀለችዉ ። ቁርጥ እነሱን መሰለች ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 55) እንዲህ ብሎ ገልጿታል ።

**ማህበራዊ አሳሳል**

ወጣት ፣ ያላገባች ፣ የሴቶች የዉበት ሳሎን ከፍታ እየሰራች የምትተዳደር ።

**ስነ ልቦናዊ አሳሳል**

ሃሳቧን የማትቀይር የነ መንበረ የአክስት ልጅ መባልን ሳይሆን እህት መሆንን አብዝታ ትመኝ ነበር ።

**ዶክተር ጀምበሩ**

**አካላዊ አሳሳል**

" ሀሳቡን በንግግርና በፅሁፍ ከማይገልፅ ፣ አንብቦ ከማይረዳ ተማሪ ጋር መዳረቅ ሰልችቶኛል ። እንደምታየው አርጅቻለሁ ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 22) እንዲህ ሲለን ዶክተር ጀምበሩ እራሱን እያስተዋወቀ ነው ። እናም የእድሜ ባለፀጋ መሆናቸውን ያስረዳል ። " ያለህ የአከሻ ነፍስ ነው ። " ዶክተር ጀምበሩ ከሲታ ፊታቸዉን ቅጭም አድርገው አረቄውን ተጎነጩ ። " (ችካል እና እርምጃ ገፅ 136) ዶክተር ጀምበሩ ቀጠን ያለ ተክለ ቁመና ያላቸው እና አይናቸው ትናንሽ እንደሆኑ ያሳዉቃል።

**ማህበራዊ አሳሳል**

የተማሩ ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርነት እየሰሩ የሚኖሩ ። የትዳር አጋር የሌለው ወይም ያላገባ ። " ወንድምህ ልጅ ሳይወልድ ፣ ቤት ሳይሰራ ፣ ያለ አሻራ ፣ ያለ ዳና አለፈ ። አንተም እንደሱ ያለመጠሪያ እንዳትባክን ልጄ ፣አግባብና ዉልድ ፣ ዛኒጋባ አቁም > ብለከኝ ነበር ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 220) እንዲህ ሲል ያላገባ እንደሆነ ትዳር እንደሌለው ራሱን ያስተዋዉቀናል ።

**ስነ ልቦናዊ አሳሳል**

" የምታወራው ምንድን ነው ? እየተናገረ የሚያደነቁር እንጂ እየሰማ የሚሻሻል ስርአት አለን? ቆይ ሌላውን ተዉትና የእኛን ዩኒቨርሲቲ ተመልከቱ ፣ ማን ይሰማል? በመጀመሪያ ደረጃ፣ በፖለቲካዊ አስተዳደሩና በዩኒቨርስቲው መካከል ምን ልዩነት አለ? ፓርላማው በብሄር ፣ የዩኒቨርስቲው ፕረዚዳንቶች ሹመት በብሄር ። የተለየ ሀሳብ እንደጦር ይፈራሉ ። የተቃወምካቸዉ እንደሆነ ካልቆረጡህ ያቀጭጩሀል ። ከሰገድክላቸዉ ሁሉ በእጅህ ሁሉ በደጅህ ። "( ችካል እና እርምጃ ገፅ 224) ይህን ሲል ዶክተር ጀምበሩ ምኞታቸው ህልማቸው በብሄር በጎሳ መከፋፈል እንዳይኖር ሁሉም እኩል እንዲሆን እንደነበር ያመለክተናል።

**ዶክተር ይመር**

**አካላዊ አሳሳል**

እድሜያቸው በሰል ያሉ ቁመቱ ረዘም ያሉ ጥርሱ ጥቁር እና ሰፊ ድዱ ያለው ፈገግታዉ የማይስብ ናቸው ።

**ማህበራዊ አሳሳል**

የተማሩ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ክፍል ሀላፊ ሆነው እየሰሩ የሚኖሩ ናቸው ።

**ፕሮፌሰር ጌታቸዉ**

**አካላዊ አሳሳል**

*መፅሀፉ ላይ እንዲህ ብሎ የሚገልፃቸዉ የለም ነገር ግን አጥኝዋ እንደተረዳችዉ እድሜያቸው የገፋ ፣ኑሮ ፊታቸዉን ያበላላዘዉ ፣ቀጭን ሲራመዱ ጎንበስ ያሉ ናቸው።ኑሮ ፊታቸዉን ያበለዘዉ ያልኩበት ነገር ገና ልጅነቱን ሳያጣጥም ልጅ አሳዳጊ ሆኖ የቤተሰብ ሀላፊነትን የተሸከመ በመሆኑ ነው።"ገጠር ዉስጥ አባወራ በሌለው ጎጆ አራት ከአስራ ሶስት ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ታሳድግ ስለነበረች እናት ሞት። መራቧ ሳያንሳት ለልጆቿ የምትዘግነዉ አጥታ በቸነፈር ስለሞተች እናት። በንዳድ እየተንዘፈዘፈች በሞቷ አልጋ ላይ እጅህን ይዛ ፣'የወንድሞችህንና የእህትህን ነገር አደራ?በምድር የሰጠሁህን በሰማይ እጠይቅሃለሁ 'ብላ ፣አይኖቿን አይንህ ላይ ተክላ ስለሞተች እናት። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 173)ይገልፅልናል።*

**ማህበራዊ አሳሳል**

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ሞያ እየሰሩ የሚኖሩ ናቸው።

" ዶ/ር ጀምበሩ እና ፕሮፌሰር ጌታቸዉ የሚተዋወቁት ከ1960ዎቹ አጋማሽ ነው ፤ መሬት ለአራሹ ዘመን ፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪ እያሉ። በ1965 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲመረቁ ሁለቱም በመምህርነት ተቀጠሩ ።"( ችካል እና እርምጃ ገፅ 138) የተማሩ እንደሆነና የትምህርት ደረጃቸውን ያሳዉቀናል ።

**ግብረ ገባዊ አሳሳል**

መልካም ፣ ትሁት፣አደራዉን የሚወጣ በልጅነቱ እናቱ አራት እህትና ወንድም ሰጣዉ አደራ ብላው ስትሞት የእናቱን አደራ ተቀብሎ እህትና ወንድሞቹን አሳድጎ አስተምሮ ሁሉንም ደረጃ ላይ ያደረሰ ታማኝ ለቃሉ የሚኖር ነው ።

**ስነ ልቦናዊ አሳሳል**

የቤተሰብ ፍቅር ያለው እህትና ወንድሞቹን እንደናትም እንደ አባትም ሆኖ ደረጃ ላይ ያደረሰ።

***መሀሪ***

**አካላዊ አሳሳል**

ወጣት ደንደን ያለ የሰዉነት አቋም ያለዉ የኑሮ ምቾት ፊቱን ያጣራው ነው ።

**ግብረ ገባዊ አሳሳል**

" ለፖለቲካ የሚሆን ተፈጥሮ የለዉም፣ ሰብዐዊነቱ ይጎላል በጣም ጥሩ ሰው ነው ። ከእሱ ጋር ስሆን በእናቴ እቅፍ ዉስጥ ያለሁ ያህል ምቾት ይሰማኛል ። ይናፍቀኛል ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 154) ይህን ስትል ፅጌ መሀሪን እየገለፀችልን ነው ። ከእናት የሚወዳደር ክብር የሚሰጥ ሰው ፣ ለሰው የሚመች ፀባይ ያለው ነው ።

**ማህበራዊ አሳሳል**

ያላገባ የፅጌ የፍቅር ጓደኛ ፣ ዉጭ ሀገር ድረስ በመሄድ መስሪያ ቤት ዉስጥ የሚሰራ ነው። " መሀሪ አዲስ ተመልሶ በዉጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በትልቅ የሀላፊነት ቦታ ላይ መስራት እንደጀመረ ፤የሀገሪቱ ሁኔታ በፍጥነት እየተለወጠ መጣ ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 207) የስራ ሁኔታውን ገልጾልናል ።

**ስነ ልቦናዊ**

"መሀሪ ለስላሳ፣ የአየር ፍራሽ ነው ፤ይመቻል ። ምቾት ሆኖ እንዳሻት እንድትናገር ይተዋታል ፤ስትፈልግ ሳቋን፣ስትፈልግ ብቸኝነቷን ፣ ስትፈልግ ልቅሶዋን ፣ ስትፈልግ ፈንጠዝያዋን፣ የፈለገችውን፣ ያሻትን እንድትኖር የምቾቷ ቃሬር ነው ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 153) ይህን ሲል የመሀሪን አስተዋይነት ለሰው ነፃነትን የሚሰጥ የዋህ እንደሆነ ነግሮናል ።

## 3.4 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከግጭት አንፃር

ሰው ከሰው ጋር በምንለው የግጭት አይነት ዉስጥ ተሰማ እና ዶክተር ይመር ይጋጫሉ ። የሚጋጩትም ተሰማ ነፃ የትምህርት ዕድል አግኝቶ ሊሄድ ሲል ዶክተር ይመር ደግሞ መሄድ የለብህም በሚል ምክንያት አለመስማማት ይፈጠራል ። " ሁለተኛ ዲግሪ እያለህ ፣ ሌላ ሁለተኛ ዲግሪ ቅንጦት ነው ። "መማር ቅንጦት የሚሆነው እንዴት ነው ። " በሚል ቃለ ምልልስ ገፅ 24 እናገኘዋለን ። መንበረ እና አቶ ተመስገን ፣አቶ ተመስገን ባልወልድሽም ልጄ ነሽ ይላት ነበር ። አሁንም ያደረጋትን ነገር ለሰው ላለማሳወቅ እና እሷም የረሳችዉ አስመስሎ ልጄ ሲላት አትበለኝ በማለት በተፈጠረው ክስተት ይጋጫሉ ። " ልጄ አትበለኝ ! ልጄ አትበለኝ አባቴ አይደለህም ፣ አባት ልጁን ይደፍራል ? አባዬ ፣ እማዬ አልታመምኩም የደፈረኝ እሱ ነው ። ያረገዝኩት ከሱ ነው ። "ገፅ 299 ላይ እናገኘዋለን ። ዮዲት እና አቶ ተመስገን በሀሳብ ባለመስማማት አለመግባባት ተፈጥሯል ። መንበረ አጎቷ እንደደፈራት አራት አመት ያክል ደብቃዉ የቆየችውን ሚስጥር ስትናገር አቶ ተመስገንም ቤተሰቦቿ እንዳያዉቁ ኧረ አሟት ነው ባለ ጊዜ ዮዲትም የደበቀችዉን ሚስጥር አወጣችዉ ። ገፅ 300 ላይ እናገኘዋለን ። ወ/ሮ እልፍነሽ እና አቶ ተመስገን፣ የአቶ ተመስገን የቀለለ /የተናቀ ስራቸውን ድርጊታቸውን በሰሙ ጊዜ ወ/ሮ እልፍነሽ ራሳቸውን መቆጣጠር ሲያቅታቸው፣ ያሳደገቻትን የልጇን ፍቀረኛ ደፍሮ በሌላ ሲያስመስል መቆየቱንና በዚያው ሰዓት ዮዲትንም ሊደፍራት ሙከራ አድርጎ ሳይሳካለት እንደቀረ ስታዉቅ ጠገራ (ምሳር ) በተባለው ይመቷቸዋል። በሃሳብም በምንም ካለመስማማትም አልፎ ህይወት እስኪያልፍ ተጋጭተዋል ። ገፅ 300 ላይ ገልጾታል ። ተሰማ እና አመንሲሳ ኖርዌይ ዉስጥ የኦሮሞ ኮሚኒቲ ፕረዚዳንት ከሆነው ጋር ተሰማ ኖርዌይ በሄደ ሰሞን በቤት ስልኩ ተደዉሎለት ሲያወሩ በኦሮሚኛ አዋራኝ ሲለው ተሰማ ደግሞ ኦሮሚኛ አልችልም እናቴ የመንዝ ሰው ናት አማራ አባቴ ደግሞ ኦሮሞ ነው ። የጋራ ቋንቋቸዉ አማረኛ ስለሆነ አፍ የፈታሁበት በሱ ነው ሲለው እንዴት የአሰላ ልጅ ሆነህ ኦሮሚኛ አታወራም ባለው ጊዜ ከዚህ በፊትም እንደዚህ አይነት ጥያቄ ቀርቦለት ስለሚያውቅ በዚህ የተነሳ አለመግባባት ይፈጠራል ።

ሰው ከራሱ ጋር በሚለው ዉስጥ ደግሞ ተሰማ መንበረ ስልክ አላነሳለት ባለች ጊዜ ከራሱ ጋር ይጋጫል ። ለምንድን ነው ስልክ የማታነሳዉ ? መቅረቴን ብትሰማስ ? ምክንያቱን መጠየቅ የለባትም ? መቼም ሌላ አፍቅራ አይሆንም ። እያለ ገፅ 67 ላይ ይገልጻል። መንበረ ባጋጠማት ችግር የተነሳ ለፍቅረኛዋ ለተሰማ ስልክ አንስታለት አታዉቅም ። ሲመጣ የምለው ምንድን ነው ? የሆነውን ሁሉ እነግረዋለሁ ?

ለምን አልነገረዉም? ለእሱ ካልተናገርኩ ለማን ልናገር ?

ግን ምን ብዬ ? ይህ ለሰው ይነገራል ?

እሱ ሰዉ ነው እንዴ ? ግን ምን ይለኝ ይሆን ?

የፈለገውን ይበል እነግረዋለሁ። ለእሱማ አልደብቀዉም ቢጠላኝም ይጥላኝ ። እያለች ከራሷ ጋር ስትከራከር ገፅ 49ላይ ያሳየናል ። ፅጌ የመንበረ ልጅ በሞተባት ጊዜ ቤቷ ሄደዉ ተሰማ ለመንበረ ያለዉን እንክብካቤ ምን ያህል እንደሚወዳት እንደማሳሳላት ባየች ጊዜ ለምን እኔን አይወደኝም ማለት ነው ። ይህንን ፀባይ ከእኔ ጋር ሲሆን አላየውም ከሷ ጋር ሲሆን ግን እንዴት ስትል ፣ እንኳን መጣሁ እንዴት አባቱ እንደሚቅለሰለስ አየሁት ። ለካ የአንዱ እሾህ ለሌላው ፍራሽ ነው ። ልክ መሀሪን እኮ ነው የሆነላት why do I care, anyway? (ግን እኔ ምን ቸገረኝ ! እያለች ስትጋጭ ገፅ 276 ላይ ያሳያል ።እዉነት ምን እየሆንኩ ነዉ?ቀናሁ ማለት ነዉ? ያልነገረኝ ለምንድን ነዉ?ቢነግረኝስ ምን ይፈጠራል? መዋሸቱ ግን ያናድዳል።...ምን አየሆንኩ ነዉ? እንደተናደድኩ ማወቅ የለበትም። "

ፈገግ አለች። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 235) ይህም ሲሆን ፅጌ በቅናት የተነሳ ከራሷ ጋር ስትጋጭ ያሳየናል።

ተሰማ አመንሲሳ የኦሮሞ ህዝብ መብትና ነፃነት የሚረጋገጠው በኦሮሞ ህዝብ ብቻ ነው ። ባለው ጊዜ ችግሮቻችንን በብሄር መነፀር ብቻ ማየት የምናቆምበት ጊዜ ይመጣ ይሆን ? አዲስ አይን የምናወጣው መቼ ነው ? ሲል ሲጋጭ በገፅ 39 ላይ እናገኘዋለን። ፅጌ ከዉስጧ የእዉነት የማፈቅረው ማንን ነው? እኔ የምፈልገው ምንድን ነው ? የምፈልገው ማንን ነው ? እያለች ከራሷ ጋር ስትጋጭ ገፅ 284 ላይ እናገኘዋለን ።

ሰው ከማህበረሰቡ ጋር በሚለው ዉስጥ ደግሞ ተሰማ ዩኒቨርሲቲ ማስተማር እንደጀመረ በዩኒቨርስቲው ዉስጥ የሚያስተምሩና በዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዉስጥ የሚሰሩ የአማራ አብርሄ ተወላጆች ለአማራ ህዝብ መብት የሚታገል የፖለቲካ ድርጅት ለማቋቋም እየሰሩ ባለበት ጊዜ አብሯቸው እንዲሆን ሲጠይቁት" እኔ በብሄርና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ፖርቲ ለመመስረት አልሆንም ፤ ለማፍረስ ካልሆነ። ስለዚህ ተዉኝ።" ሲል ገፅ 39 ከማህበረሰቡ ጋር ሲጋጭ እናያለን ።ሌላው ደግሞ ተሰማ ኖርዌይ ዉስጥ እያለ አመንሲሳ ከሚባለው ህዝብን ወክሎ ከተላከ የኦሮሞ ኮሚኒቲ ፕረዚዳንት ጋር እንዲህ ሲሉ " እሱ የጎንደር ሰው ነው " ብሎ አይናፋር ሳቅ ሳቀና ፣ "እኔ የማወራልህ እንኳን ስለ ኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ሳይሆን ፣ ስለ ኦሮሞ ኮሚኒቲ ነው ። "

"አዉ ፤ ስለኦሮሞ ኮሚኒቲ እንኳን አልሰማሁም ። "

" የኦሮሞ ህዝብ መብትና ነፃነት የሚረጋገጠው በኦሮሞ ህዝብ ብቻ ነው ። "

" እኔ እንኳን እንደዛ አላምንም ። ኢትዮጵያ ዉስጥ አንድ ብሄር ብቻውን ተደራጅቶ ስለመብቱ ሊጠይቅ ይችላል ፤ የሚደርስበት ጭቆና እንዲገለጥና ትኩረት እንዲያገኝ ሊያደርግ ይችላል ። በብቻ ድርጅቱ ታግሎ ፣መብቱን ሙሉ በሙሉ ማስከበር ግን ይችላል ብዬ አላምንም ። አንድ ብሔር "መብቴ ይከበር " ብሎ ስለታገለ መብቱ አይከበርም። መብቱ የሚከበረው የኢትዮጵያ ብሔሮች በሙሉ "መብቱ ይከበር ' ብለው ሲታገሉ ነው ፤ አንዱ ለሁሉም ፤ ሁሉም ለአንዱ ።

"ይህ "የኦሮሞ ህዝብ ታግሎ መብቱን ለማስከበር አይችልም ' የሚል የቆየ የነፍጠኞች ትርክት ነው ። ይህን ትርክት ለመለወጥ ደግሞ የእኛ የተማርን የኦሮሞ ልጆች ሀላፊነት ነው ። ይህን ሲባባሉ ተሰማ ከማህበረሰቡ ጋር ሲጋጭ ገልጾልናል።

ሰው ከተፈጥሮ ጋር በሚለዉ ግጭት ዉስጥ ደግሞ ተሰማ ኖርዌይ ሄዶ በነበረበት ጊዜ የሄደው ጥር ወር ላይ ቢሆንም ሀገሩ ክረምት ነበር ። " ድንቄም ክረምት፣ ክረምት ያለ ልምላሜ" ሲል አሰበ የመተዋወቂያ ፕሮግራማቸው ላይ የዓለም አቀፍ ተማሪዎች ቢሮ አስተባባሪ" አለመታደል ሆኖ በክረምት መጣችሁ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኖርዌይ ለሚመጡ ተማሪዎች ጥር የሚመረጥ ጊዜ አይደለም ፣" ያላቸውን አስታዉሶ ። እንዲህ ሲል ገፅ 35 ላይ ከተፈጥሮ ጋር ሲጋጭ እናየዋለን ።

## 3.5 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከመቼት አንፃር

ችካል እና እርምጃ አጠቃላይ ቦታ - የልቦለዱ ታሪክ የተፈፀመበት አጠቃላይ ቦታ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሲሆን ዉሱን ቦታዎች ደግሞ - አዲስ አበባ 6ኩሎ ዮኒቨርሲቲ ግቢ ወስጥ ሲሆን ጠዋት ዶክተር ይመር ቢሮ ዉስጥ ተሰማ ኖርዌይ ለትምህርት እንዳይሄድ የተከለከለበትን ምክንያት ለመጠየቅ ሄዶ ፣"አግባብ አይደለም ፤በደል ተፈፀሙብኝ ካልክ ወደ ላይ አቤት ማለት ትችላለህ።"አለው ፣ በማናለብኝነት እየተመፃደቀ ። "በተማርከዉ ምን ሰራህበት? በመማርህ ሀገራዊ ምን ጠብ አለለት ? አሁን ማን ይሙት ለዩኒቨርስቲው ወይስ ለሀገር አስበህ ነው? ኖርዌይ ሄደህ እንደማትመለስ አንተም እኔም እናዉቃለን ። ሚስት የለህ ድስት የለህ ! ምን ቀረኝ ብለህ ትመጣለህ ? "እያለ በንቀት ፈገግ አለ ።

" ስማ ዶክተር እኔ አንተን ብሆን በአሜሪካ ታሪክ ላይ የሶስተኛ ዲግሪ ጥናቴን ሰርቼ ይህን አልናገርም ነበር።አዉቅሀለሁ አኮ! ካድሬ እንደሆንክ አዉቅሀለሁ ። ረዥም እጅ አለህ ፤ አዚህ ወንበር ላይ ያስቀመጠህ ረዥም የካድሬ እጅህ ነው ። ላናግርህ የመጣሁት እንደካድሬነትህ ሳይሆን፣ ፊደል እንደቆጠረና ሀላፊነት እንደሚሰማው ሰው ልታናግረኝ እንደሁ ብዬ ነው ። "

"ለሀገር መስራት ካድሬነት ከሆነ፣ሞቼም ካድሬ እሆናለሁ ። "

"ለሀገር መስራት ካድሬነት፣ካደሬነትም ለሀገር መስራት አይደለም ። ካድሬ ኖረም ሞተም ለባለወንበሩ እንጂ ለባለ ሀገሩ ብሎ አይደለም ። "

"ዉጣልኝ ከቢሮዬ ! "

"ከቢሮዬ? "አስላቅ ሳቅ ጋር በሩን በእርጋታ ዘግቶ ወጣ ፣።(ችካል እና እርምጃ ገፅ 25) እንዲህ ሲሉ ቢሮ ዉስጥ መሆኑን ያሳዉቃል ።

ኖርዌይ - ተሰማ ለትምህርት ኖርዌይ ሲሄድ ኖርዌይ ፣ ትሬንዳይም ሲገባ የጥር ወር ጨለማ (ክረምት) በስካንዴንቪያን ሀገሮች ከህዳር እስከ መጋቢት ያሉት ወራት ቀዝቃዛና በረዷማ ናቸው ። ገፅ 35 ተሰማ ኖርዌይ ለሶስት ዓመት ቆይቶበታል።

አዳማ -ዮዲት አረብ ሀገር ደርሳ ከተመለሰች በኋላ አዳማ የሴቶች የዉበት ሳሎን ከፍታ የምትሰራበት ።"ለአራት አመት የሰራችበትን አባቷ ዘንድ ትልክ ነበር ። አቶ ፈይሳ አንድ ፣ ሁለት ብለው ያጠራቀሙበትን ፣በስሟ የተከፈተ የባንክ ደብተር አስረከቧት ። አዳማ የሴቶች የዉበት ሳሎን ከከፈተች አመት አለፋት ። አዳማ ዉስጥ የታወቀ የቁንጅና ሳሎን ሲባል ፣በመጀመሪያ የሚጠራው ፣ 'ዮዲት የዉበት ሳሎን ' ሆነ ።

አሰላ - የመንበረ ቤተሰቦቿ የሚኖርበት ነው። " አሰላ ከተማ ገና ከእንቅልፏ እየነቃች ነው ፤ ጉም እንደለበሰች ታዛጋለች ። የጭላሎ ተራራ ቀዝቃዛ ትንፋሽ ከተማው ላይ እንደተኛ ነው ። ያካፋል የመንበረ አባት በወንድማቸው የጨርቃጨርቅ መደበር ዉስጥ ፣ በልብስ ስፌት መኪናቸው ላይ ይተከዛሉ ።ውሱን ቦታ ደግሞ አዳማ ዉስጥ ሆኖ እርዝመት ባለው አጥር የታጠረ ሀጂ ሱሌማን አጥር ግቢ ዉስጥ ሚያዝያ 20 ረፋድ አራት ሰአት ላይ ህፃናት ማቆያዋ መጥተው ከህፃናት መካከል አንዱ በኮቪድ እንደተያዘ ሲነግሯት ። ገፅ 214 ላይ እናገኘዋለን ።

የዚህ ልቦለድ አጠቃላይ ጊዜ 2012 ነው ። " የአቶ አመንሲሳ ልጅ የሚዉለዉ እዚህ ፣አንቺ ጋ ነበር ? "

"አዎ። ገመቺስ ምን ሆነ ? ሰላም አይደለም ? " መንበረ ደነገጠች።

"ከፍተኛ ችግር ተፈጥሯል። "

"ምንድን ነው ? ምን ሆሁ ገመቹስ ? ትላንት ደዉዬ ሰላም ነው ብለዉኝ ነበር እኮ ። "

" አባቱ የኮሮና ቫይረስ ተገኝቶባቸዋል። "

ወገቧ እምሽክ ሲል ተሰማት።

"እና ገመቹስ ... "

"አዎ! ገመቹስም ቫይረሱ ተገኝቶበታል። " እንዲህ ሲለን አጠቃላይ ጊዜን ገልጾልናል ።

ውሱን ጊዜዉ ደግሞ መጋቢት 5/05/2012 ኮቪድ የገባባት ጊዜ ነው ።

ችካል እና እርምጃ ማህበራዊ ሁኔታው ምን ይመስላል?

በዚህ ልቦለድ ዉስጥ ማህበራዊ ሁኔታው 2012 ዓ.ም ጊዜ ፖለቲካውን በተገቢው ሁኔታ ገልጾታል ። አሁን ያለዉን ሀገራዊ ጉዳይ በዘር ፣ በቋንቋና በሀይማኖት ዉስጥ ያለዉን ግጭት እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ያለዉን የስልጣን ሽኩቻን ፣ ዘረኝነትን ፣ በቋንቋ በአንድ አካባቢ ዉስጥ የዛን አካባቢ ቋንቋ ተናጋሪ ካልሆነ የሚገለገልበትን ሁኔታ ሁሉ ያብራራል።ስለ ኮሮናዉም በጥሩ ሁኔታ ተዳሷል ። ኮሮና በሀገራችን ላይ ያስከተለውን ጉዳት የሰው ህይወትን አጥፍቷል ፤ ማህበራዊ ኑሮን አራርቋል ፤ ሰው ከሰዉ ጋር እንዳይገናኝ ሆኗል ፤ ይህም ሲሆን መንበረ የስራ መስኳ ተዘጋባት ፤ የመንበረን ልጅ አጉድሏል ይህን ሁሉ ያለውን ነገር በተገቢው ሁኔታ ታይቷል ። አለባበሳቸው በሚታይበት ጊዜ አሁን ላይ ያለውን ማህበራዊ ሁኔታ ከጊዜው ጋር ያለ መሆኑን ይገልጻል። የተለያየ ነገር አይታይበትም ። ኢኮኖሚያዊ ሲታይ ደግሞ ፅጌ ላይ ትንሽ የተጋነነ ነው ። ነገር ግን ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ፤ የፍቅር ጓደኛዋም የሀገር ዉስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰራተኛ ነው ። ፍቅረኛዋ ከሌሎቹ የተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዳለው እና መኪናዋም ስጦታ የተሰጠችው ነው ። አመጋገባቸዉ ላይ ትንሽ የተጋነነ ነገር ይታይበታል። አሁን ካለዉ ከጊዜው አንጻር ሲታይ በፊልም ላይ ካልሆነ እና ትንሽ የጤና ችግር

ያለበት ሰው ካልሆነ አንድ ሰው ሲናደድ በጠዋት ተነስቶ አልኮል ጋር ይህን የሚያክል ግንኙነት ያለው የለም። ሌላ ደግሞ ሁሌም ከወንዶች ጋር አብራ እያመሸች መጠጣት ፤ ፅጌ የመንበረ ልጅ ሞቶ ሊደርሱ የሄዱ ጊዜ ተሰማ መንበረን ሲንከባከብ አየሁ ብላ ተናዳ ወጣ መኪናዋ ዉስጥ ተቀምጣ አልኮል መጠጣቷ አሳማኝ አይደለም ። ምክንያቱም ከተሰማ ጋር በባሏ ላይ ጥሩ ያልሆነ ስራ ሰራችበት እንጂ ከዛ ያለፈ የትዳር አጋሯ አይደለም እዚህ የሚያደርስ ነገር የለም።

### 3.6 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከጭብጥ አንፃር

የችካል እና እርምጃ ልቦለድ አብይ ጭብጥ ፣ የሆነ የተቸከልንበት ነገር አለ እሱን ነገር ነቅለን ወደፊት እንራመድ የሚል ሲሆን ከዚህ መካከልም በዘር በቋንቋ ፣ በቋንቋ ምክንያት የሚመጡ የዘር ክፍፍሎች አንደኛው የትግራይ ቋንቋ ተናጋሪ አንደኛው የኦሮምኛ ተናጋሪ አንደኛው የአማርኛ ተናጋሪ ናቸው ። ይህም ሲሆን የአንድ ብሄር የበላይነት እንተው ሁሉም ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉት ብሄሮች ሁሉ እኩል ናቸው ነው ። አንዱ ከአንዱ አይበልጥም አንዱ ከአንዱ አያንስም ሁሉም ለዚች ሀገር የሚሰጡት አስተዋጽኦ አለው ነዉ ። ለምሳሌ ተሰማ የእናቱ ወገኖች አማራ የአባቱ ወገኖች ደግሞ በኦሮሞ ይመጡበታል ። ስለዚህ በዘር በጎሳ ተቸንክረናል ከዚህ ነቅለን ወደፊት እንራመድ ሁላችንም አንድ እንሁን ለኢትዮጵያ እናስብ ለህዝቦቻችን ፤ ለተራቡት ህዝቦቿ እናስብ ነው ። "ትላንትን መለወጥ የሚቻለው በመርሳት ሳይሆን ተጋፍጦ በማሸነፍ ነው ። " ይህም ሲባል ከድሮ ጀምሮ በነበር ህብረተሰቡ ታዉሯል ። አሉ ነበር የሚለዉን ነገር ማህበረሰቡ መተው እና ወደ አንድነት መራመድ አለበት ። " ወንጀለኞች ናቸው ? ከሀዲ ነህ ! እነሱ በከፈሉት መሰዋእትነት እኮ ነው እዚህ የደረስከው? ብልጽግና ሆነህልኛላ? በደምብ ተደምረሀል ። " (ችካል እና እርምጃ ገፅ 212) ፅጌ እንዲህ

ስትል ከኋላቀር አስተሳሰቧ እንዳልተፋታች ነው የሚነግረን ። " መቼ ይሆን በማህበረሰባችን ከልማድ ካቴናዉ ወጥቶ በእዉቀት የሚመራው? ልማድን እዉቀት ካልገራዉ ማነቆ ነው ፤ እግረ ሙቅ ። ይህም ለምሳሌ ፅጌ ለወንድሟ ስትከራከር ነበር ። ተምራም እንኳን ከኋላ ቀር አስተሳሰቧ ልማዷን አልተወችም ። " ልምድ ያለመለወጥ ችካል ነው ። " (ችካል እና እርምጃ ገፅ 226) ይገልጽልናል ።

"ያልተሰማኝንና የማላምንበትን በይሉኝታ የማልናገር መሆኔን ታዉቂያለሽ ። በርግጥ ከልማድ መፋታት ከባድ ነው ። በተለይ ለእኛ ። "

" ለእኛ ስትል? "

"ኢትዮጵያውያንን ፣ ያገሬን ልጆች ማለቴ ነው። ለዚህ አይመስልሽም መለወጥ ያቃተን ? ማህበረሰባዊ ለዉጥ ለማምጣት ግለሰባዊ ልማዳችንን መለወጥ የመጀመሪያ እርምጃ መሆን አለበት ። "( ችካል እና እርምጃ ገፅ 256) ተሰማ ለፅጌ ይህን ሲላት ከአጉል ልማዷ እንዳልተፋታችና መጀመሪያ ሁሉም ራሱን ከአጉል ልማድ ነፃ ማድረግ እንዳለበት እያስረዳት ነው።

ንውሳን ጭብጥ የቤተሰብ ፍቅር እና ታማኝነት የፕሮፌሰር ጌታቸዉ በመሬት ላራሹ ጊዜ የእናቱን አደራ ተቀብሎ ' የወንድሞችህን እና የእህትህን ነገር አደሮ፣በምድር የሰጠሁህን በሰማይ እጠይቅሃለሁ "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 173) ባለችው ጊዜ ያንንም አደራ ተቀብሎ ለ15 አመት አብሮ ሆኖ ልጆችን አሳድጎ ሁሉንም ደረጃ ላይ አድርሷቸዋል። የተሰጠውን አደራ በታማኝነት ተውጧል ።

የጓደኛ ፍቅር በተሰማና በዶክተር ጀምበሩ ውስጥ ይታያል ። ይህም ማለት ተሰማ ነፃ የትምህርት ዕድል አግኝቶ በትምህርት ክፍሉ ሀላፊ ሲከለከል ። " ዶክተር ጀምበሩ ብቻ ናቸው ፣ " በሀገሪቱ የተቸነከረችበት አስተዳደራዊ ስርአት ሲበድልህ ፣ሙብትህ ሲረገጥ ማፈንገጥ ፣ ጉዱ ካሳን መሆን ያስፈልጋል ። ወደ ሲኦል በተቆፈረ ቦይ የሚፈስ እንደምን ገነት ሊደርስ ይችላል?' ያሉት ። (ችካል እና እርምጃ ገፅ 33) ይህን ሲለን ዶክተር ጀምበሩ ለጓደኛው ያለዉን ፍቅር ያሳያል ።

የሃገር ፍቅር ደግሞ ተሰማ በእናቱ እና በአባቱ በኩል ያሉት ወገኖች በየ ብሄራቸዉ እንደራጅ ብለው ከአንዴም ሁለቴ ሲጠይቁት ተሰማ ግን ለየትኛው ልሁን ተዉኝ አልችልም አለ። በብሄርና በቋንቋ መከፋፈልን አብዝቶ የሚጠላ በአንድነት በፍቅር መኖርን የሚመርጥ የሀገሩን መከፋፈል ሳይሆን አንድ መሆኗን የሚወድ ነው ። "እኔ ለማለት የፈለግኩት ግን ሌላ ነው ። እናቴ የመንዝ አማራ ናት ። አባቴ ደግሞ የአርሲ የኦሮሞ ። ለእናቴ ወገኖች ወይስ ለአባቴ ወገኖች ልደራጅ ? እኔን መሰሎች ይዛችሁ በብሔር ለመደራጀት ካሰባችሁ ስራችሁ የግብር ይዉጣ ይሆናል ። "የዉጭ ጉዳዩ ሰዉዬ ሊያሳምኑት ይችላሉ ጨያላቸዉን ሀሳቦች እያነሳ ሞከረ ። አልቻለም ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 40)የ ገልጾታል ።

## 3.7. ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ከአንፃር አንፃር

በችካል እና እርምጃ ልቦለድ ዉስጥ ምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለፀው የሚጠቀመው ሁሉን አወቅ አንፃር ነው ። በልቦለዱ ዉስጥ ተራኪው የእያንዳንዳቸዉን ታሪክ ያዉቃል ። የተሰማን እና የመንበረን "ቶሎ ቶሎ ሂዱ እንዳይረፍድባችሁ ። ደግሞ ነግሬሀለሁ ! (ችካል እና እርምጃ ገፅ 7) ላይ የመንበረንና የተሰማን አብሮ አደግ ጓደኛሞች እንደሆኑ ይነግረናል ።የተሰማ እናትና የመንበረ ቤተሰቦች "ከመንበረ ቤተሰቦች ሌላ የተሰማን እናት በእሮግማን የተለወሰ አነጋገር ችሎ የተጎራበታቸዉ የለም። ወይዘሮ ወርቄ ስሞታ አንጠልጥለው የሚመጡ ጎሮቤታቸዉን፣"ምነው የአፋን ትታችሁ የልቧን ንፅህና ብታዩላት ? እናት በልጇ መዓት ትጠራለች ? ልምድ ሆኖ እንጂ ለልጆቿ መቅሰፍት መመኘቷ ይመስላችኋል? እያሉ ብዙ ጊዜ አስታርቀዋቸዋል። "(ችካል እና እርምጃ ገፁ 48) የተሰማና የመንበረ ቤተሰቦች የሚዋደዱ እንደሆኑ አብረዉ የኖሩ ተሰማ እና መንበረም ሁለቱንም እማ ብለው ጠርተዉ ያደጉ፤ የተሰማን እናት በፀባይ ተረድተው የአፋን ሳይሆን የልቧን ቀናነት ተረድተው ፤ ተቻችለው በአንድ ሰፈር እንደሚኖሩ እንደሆኑ ነግሮናል።

የዶክተር ጀምበሩን እና የተሰማን ግንኙነት ተሰማ ገና ተማሪ እያለ ጀምሮ ለመመረቂያ ፅሁፍ በሚሰራበት ጊዜ መረጃ በሚያሰባስብበት ወቅት ጀምሮ እንደሚተዋወቁ ነግሮናል ። "ተሰማ እባላለሁ ። የታሪክ ትምህርት ክፍል የአራተኛ ዓመት ተማሪ ነኝ ። የመመረቂያ ጥናቴን በአክሱም የድንጋይ ላይ ፅሁፎች ላይ እየሰራሁ ነው። እርስዎ በዚያ ላይ ስለሰሩ እንዲያማክሩኝ ፈልጌ ነው።" ድምፁ ይንቀጠቀጣል ፤ ድንጋጤው ገና ሙሉ ለሙሉ አለቀቀዉም ።

"ዛሬ አርብ ነው ? "

"አዎ ፤"

"ነገ አራት ሰዓት ና። "

"አመሰግናለሁ ፤"ገፅ 18 ላይ ገልጾልናል ።

የፅጌ እና የመህሪን ግንኙነት እንዲህ ሲል ይነግረናል። "...የመጀመሪያ ዲግሪየን ስጨርስ ነው ፤ይህንን መኪና የሰጠኝ ። ወንድሜ ጉኡሽ ጋር አዘዉትረዉ ይገናኙ ነበር ፤ እኔም የተዋወቅኩት ገና ዩኒቨርሲቲ ሳልገባ አስራ ሁለተኛ ክፍል ሆኜ ነው ። ቅዳሜ ቅዳሜ እኛ ቤት ነበር የሚያመሹት ። በነገራችን ላይ የምኖርበት ቤትም የመህሪ ነው ። " (ችካል እና እርምጃ ገፅ 154)ይህን ሲለን አንድ ሰፈር አብረው እንዳደጉ ከልጅነት ጀምረው እንደሚተዋወቁ እና እንደሚዋደዱ ነግሮናል።

ዶክተር ጀምበሩ እና ፕሮፌሰር ጌታቸዉ የሚተዋወቁት ገና በትምህርት ላይ እያሉ ጀምሮ የሚተዋወቁ እንደሆኑ ያሳዉቀናል ። "ዶክተር ጀምበሩ እና ፕሮፌሰር ጌታቸዉ የሚተዋወቁት ከ1960ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ነው ፤በመሬት ላራሹ ዘመን ፤ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሳሉ። በ1965 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ ትምርህታቸውን ጨርሰው ሲመረቁ፣ሁለቱም በመምህርነት ተቀጠሩ ። "(ችካል እና እርምጃ ገፅ 138)

## 3.8 ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድን ጠንካራና ደካማ ጎኑን መተንተን

### . የችካል እና እርምጃ ጠንካራ ጎኑ

በዚህ ልቦለድ ዉስጥ ድክመት ቢኖረውም። የልቦለድ አላባዉያንን በዉስጡ አካቶ የያዘ የታሪኩ ፍሰት አንባቢያንን የሚያጓጓ እና ቀልብ የሚይዝ አቅም አለው ፤በመቀጠልም በሀገራችን አሁን ላይ ያለውን የፖለቲካ ጉዳይ ፣ ማህበራዊ ጉዳይ ፣ ስለ ኮሮናዉ ጉዳይ በሙሉ ተዳሰዋል ። በጥሩ ሁኔታ ተገልፆዋል ።

የመቼት አጠቃቀሙ በጥሩ ሁኔታ ነዉ የተገለፀዉ ስለመምሸት መንጋቱን ሰዓትን ሁሉ ያካተተ ሆኖ ነው የተገለፀ። ውሱን ጊዜዉ ደግሞ መጋቢት 5/05/2012 ኮቪድ የገባባት ጊዜ ነው። ውሱን ቦታ ደግሞ አዳማ ዉስጥ ሆኖ እርዝመት ባለው አጥር የታጠረ ሀጂ ሱሌማን አጥር ግቢ ዉስጥ ሚያዝያ 20 ረፋድ አራት ሰአት ላይ ህፃናት ማቆያዋ መጥተው ከህፃናት መካከል አንዱ በኮቪድ እንደተያዘ ሲነግሯት ። ገፅ 214 ላይ እናገኘዋለን ።

## ምዕራፍ አራት

### 4.1. ማጠቃለያ

ልቦለድ የገሃዱ ዓለም ነፀብራቅ ነዉ። ደራሲው በምዕናቡ ዉስጥ ያሰባቸውን ገፀባህሪያትን በመፍጠር የተፈጠሩ ወይም ገና ይፈጠራሉ ብሎ የሚያስባቸውን ነገሮች ለገፀ ባህሪያት ስምና መጠሪያ ሰይሞላቸዉ መግቢያና መዉጫ አዘጋጅቶላቸዉ ፣በህይወት በሚያጋጥማቸው ዉጣ ዉረድ ላይ ኑሯቸዉን ለማሟላት ሲሉ የሆነ ችግር ሲያጋጥማቸው ፣ያንን ችግር ለማለፍ ሲጣጣሩ፣በሀሳብ አለመስማማት ሲያጋጥማቸው፣ የሚኖሩበት ቦታ ምቾት አልሰጣቸዉ ሲል መኖር እስከተፈቀደላቸዉ ጊዜ ለተደራሲያን ስሜትን የማጋባት አቅም ያላቸው ፣የደራሲው የምዕናብ ፈጠራ የገሃዱ ዓለም ነፀብራቆች ናቸው።

በሀገራችን ልቦለድ መፃፍ ከተጀመረበት አንስቶ አሁን እስካለበት ድረስ የተለያዩ ልቦለዶች ሁሉም የራሳቸውን አሻራ ያስቀመጡ ልቦለዶች አሉ። ከእነዚህም ልቦለዶች ዉስጥ አንዱ በበድሉ ዋቅጅራ የተደረሰው ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ ነው።

ችካል እና እርምጃ ረጅም ልቦለድ በዉስጡ ከያዛቸው የታሪክ ፣የጭብጥ ፣ የአንፃር ፣የግጭት ፣የትልም ፣የመቼት እና የገፀባህርይ እነዚህ የመሳሰሉትን ለአንድ ልቦለድ ወሳኝ የሆኑ ነገሮች በተገቢው መልኩ የተቀመጡበት ለወደፊት ለሚፃፉ ልቦለዶች ትምህርት የሚሆን በጥሩ ሁኔታ የተፃፈ ልቦለድ ነው።

## ዋቢ መፅሀፍት


ሳሙኤል ተስፋዬ። (2010)።የትወና ጥበብ። አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።

ብርሃኑ ገ/ፃዲቅ። (2008)።አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ። በረከት ማተሚያ ኋ/የተ/የግ/ማ።

ዘሪሁን አስፋው። (2005)።የስነፅሁፍ መሰረታዊያን። አዲስ አበባ። አርቲስት ማተሚያ ቤት።

(ፕሮፌሰር) ያለው እንዳወቀ ሙሉ። (2009)።የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር። ሊትማን መፃህፍት።

ጫንያለዉ ወ/ጊወርጊስ ፣ተስፋዬ ገ/ማርያም ፣አስታጥቃቸዉ ይሁን ፣እቴነሽ ካሳ እና አለማየሁ ታደሰ። (2009)።መሰረታዊ የተዉኔት አፃፃፍ መርሆዎች። አዲስ አበባ ኢትዮጵያ። በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ።